# አባቴና እምነቱ

## የአለቃ አያሌው ታምሩ የሕይወት ታሪክ

ከሥምረት አያሌው ታምሩ

ሰኔ ፳፻፯ ዓመተ ምሕረት

# አባቴና እምነቱ

## የአለቃ አያሌው ታምሩ የሕይወት ታሪክ

ሰኔ ፳፻፯ ዓመተ ምሕረት

የመጀመሪያ ዕትም

የደራሲዋ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።
© 2015 በሠምረት አያሌው

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው። የሀንን መጽሐፍ ወይም ማንኛውንም የመጽሐፉን ክፍል ለማባዛት፣ ለመገልበጥ፣ ለመቅረጽ ወይም በሌላ መጽሐፍ በሰፋት ለመጥቀስ አይቻልም። ሆኖም ግን ለጥናት ፣ ለማስተማሪያነት ለመሳሰሉት ዓላማዎች ማንኛውም ግለሰብ ፣ ቡድን ወይም ድርጅት ከዚህ መጽሐፍ ለመጥቀስ ቢፈልግ የመጽሐፉን ስም የደራሲዋን ስምና መጽሐፉ የተጻፈበትን ዓመተ ምሕረት የመጥቀስ ግዴታ አለበት።

All RIGHTS RESERVED. This book contains matarials protected under International and Federal Copyright Laws and Treaties. Any unauthorized reprint or use of this material is prohibited. No part of this book may be reproduced or transmitted in any form or by any information storaga and retrival system without express written permission from the author.

የደራሲዋ አድራሻ፣
የመ.ሣ.ቁ 3074 ኮድ 1250
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ
ተንቀሳቃሽ ስልክ፣ 091 194 8121
ኢ. ሜል አድራሻ፣ semeretayalew@yahoo.com
www.aleqa-ayalew-tamlru.org



# ምስጋና

መረጃ በመስጠትና በማሰባሰብ፣ የጀመርኩትን የመጽሐፍ ዝግጅት በርትቼ እንድጨርስ በማበረታታት፣ የጽሕፈት ሥራውን በማገዝ፣ አንብቦ አስተያየትና እርማት በመስጠት፣ የተለያዩ የማቀነባበር ሥራዎችን በማገዝ ...ወዘተ ድጋፍ ላደረጋችሁልኝ ወገኖቼ በሙሉ ከፍተኛ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።

# እኔ ልናገር

ምሁር ሊቅ ይሉሃል እውነት ሊቅ ነህ ወይ?
ቸር ለጋስ ይሉሃል ቸር ለጋስ ነህ ወይ?
ኃይለኛ ይሉሃል ኃይለኛ ነህ ወይ?
የአገር ቅርስ የአገር ሀብት አያሌው ዓባይ፡፡
ስዕውቀት ለሥራህ አለ ምስክር፣
ለቀናዒነትህ አለ ምስክር፣
ለነቢይነትህ አለ ምስክር፣
ሌሎች ያላዩትን እኔ ልናገር፡፡

ሥምረት አያሌው
የካቲት ፪፻ ዓመተ ምሕረት



# አለቃ አያሌው ታምሩ



፲፱፻፲፩—፲፱፻፺፬

"ኦርቶዶክሳዊውን እምነት፣ እውነቱን መስክር፣ የኢትዮጵያን ፍቅር፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ክብር፣ የአምላኪን ፃናናትነ፣ኃያልነት፣ ቸርነት፣ ተናገር! ተናገር! ዝም አትበል!እያለች ትቀሰቅሰኛለች፡፡ ይህ ደግሞ የግቢውንም የውጪውንም ጋኔን ያስጮኸዋል፡፡ ያስለፈልፈዋል፡፡ እኔ ግን ደንታ የለኝም ፡፡ ወንጌልን በማስተማር አላፍርበትም፡፡ ለሆዴ ብዬም ክብሬን ፣ኦርቶዶክሳዊ ፣ ኢትዮጵያዊ መብቴንም አላስረግጥም፡፡ ይህንንም ሀብቴን ፈቃደኛ ለሆነ ሁሉ ለመንፈሳዊም ለሥጋዊ ልጆቼም አወርሳለሁ፡፡ ይህ ነው እውነተኛው መንገድ፡፡

አለቃ አያሌው ታምሩ
ከምልጃ ዕርቅና ሰላም መጽሐፍ የተወሰደ

# ማውጫ

## አርዕስት ገጽ


ማውጫ vi
መቅድም ix
መግቢያ xvii

ምዕራፍ ፩
፲፱፻፲፩ - ፲፱፻፳፫
የሕጻንነት ሕይወት 1
❖ ልደትና የሕጻንነት ዓመታት 2
❖ የፈንጣጣ ህመምና አደጋው 3

ምዕራፍ ፪
፲፱፻፳፬ - ፲፱፻፴፰
የትምህርት ቤት ሕይወት 12
❖ ዲማ ፤"ለጆሮ ከባድ ለዓይን ቀላል" 13
❖ ዲማና በዓለ ተክለ አልፋ 17
❖ የየንታ ማርቆስ ህልም 22
❖ ዲማና የጣሊያን ወረራ ዘመን 26
❖ የመንግሥቱ ቅኔ ቤት 30
❖ ሸማሸንጎ መድኃኔ ዓለምና የተስቦ በሽታ ፈተና 32
❖ የከኛ ጭቃ ሹምነት 41




አርዕስት ገጽ


ምዕራፍ ፫
፲፱፻፴፱ - ፲፱፻፶፱
የሐዋርያዊ ተልዕኮ ጅማሬ 45
❖ ውስተ ሀገርከ አግዚእ ምርሀኒ 46
❖ ኢትዮጵያ ሆይ! እኔ ክብርሽን ለሌላ አልሰጥም 51
❖ ሥልጣኔ፣ ኢትዮጵያዊነት፣ የአበሻ ፈረንጆችና መሪጌታ አያሌው 60
❖ የእንግሊዘኛ ቋንቋና የብሬል ትምህርት 70
❖ መሪጌታ አያሌውና የዎች ታወር ሚስዮን ሰባኪዎች 83
❖ መሪጌታ አያሌውና የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ 89

ምዕራፍ ፬
፲፱፻፷ - ፲፱፻፷፮
ዘርፈ ብዙ የአገልግሎት ዘመናት 103
❖ የሊቃውንት ጉባዔ - ጠባቧ የአባቴ መንገድ 104
❖ ትዳርና ሥልጣነ ክህነት 127
❖ መች ተለመደና ከተኩላ ዝምድና 129
❖ ሹመት - ሺ ሞት 138
❖ አብዮቱ፣ ቤተ ክህነትና አባቴ 147

ምዕራፍ ፭
፲፱፻፷፯ -፲፱፻፹፩
ሃያ የተጋድሎ ዓመታት 171
❖ አባቴና የፍኖተ መስቀሉ ዋዜማ 172
❖ ሐምሌ ፭ ቀንና ለማያዊው መልእክት 182
❖ ዝም ብንል ታሪክ ይፋረደናል፤ እግዚአብሔርም ይጠይቀናል 190
❖ ለእግዚአብሔር እንኖራን፤ ብንሞትም ለእግዚአብሔር እንሞታለን 195
❖ የኑፋቄው መጽሐፍ 208

## ርዕስት 


| ርዕስት | ገጽ |
|---|---|
| **ምዕራፍ ፯** | |
| ፲፱፻፹፯ -፲፱፻፺፰ | |
| የሐዋርያዊው ሩጫ ማጠቃለያ | 216 |
| ❖ ሰቀለው! ሰቀለው! | 217 |
| ❖ እሁን ተመቸኝ | 223 |
| ❖ ብሔራዊ መብትን ፍለጋ | 226 |
| ❖ የእግዚአብሔር ሥርዓት ከሚዛባ የሰው ፈቃድ መለወጥ አለበት | 232 |
| ❖ ሩጫዬን ጨርሻለሁ | 241 |
| ❖ ውግዘቱን ማን ይፈታዋል? | 256 |
| ❖ ከዓለም አይደላችሁም | 265 |
| ❖ ከደማችሁ ንጹሕ ነኝ | 270 |
| ❖ በእሳቱም በውሃውም መካከል እመለግንሃለን | 277 |
| **ምዕራፍ ፰** | |
| ፲፱፻፺፱ | |
| ለንብት | 261 |
| ❖ ጾመ ማርያምና የአባቴ የመጨረሻ ቀናት | 262 |
| ❖ ፈቀደ እግዚእ ያግዕዞ ለአዳም | 288 |
| ❖ መቃብር | 293 |
| ❖ አባቴና ጥቂት ትዝታዎች | 312 |
| **ምዕራፍ ፱** | |
| ከመቃብር በላይ | 316 |
| ❖ መሆን ወይም አለመሆን | 317 |
| ❖ አሻራ | 318 |
| ❖ ሀገረ እግዚአብሔር - የአያሌው ታምሩ ኢትዮጵያ | 323 |
| መጻሕፍት | 338 |
| ፎቶዎች | 349 |
| የደራሲዋ ግጥሞች | 364 |
| አባሪ | 381 |




# መቅድም

የተከበረው አባቴ የእለቃ አያሌው ታምሩ የመንፈቅ መታሰቢያ የተደረገው የካቲት ፱ ቀን ፳፻ ዓ.ም. ነበር፡፡ በዚያ የመታሰቢያ ሥነ ሥርዓት ላይ ለተገኙ እንግዶች ያቀረብኩት አጭር ማስታወሻ ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ መነሻዬ በመሆኑ እንደ መቅድም አቅርቤዋለሁ፡፡

ክቡራትና ክቡራን!

በዚህ መድረክ ላይ ቆሜ ስለ አባቴ ስለ አለቃ አያሌው ታምሩ ያለኝን ትዝታ እንዳቀርብ አቶ ንጉሤ ሲጠይቀኝ ባገኘሁት ዕድል ደስተኛ ብሆንም የቱን ትቼ የቱን እናገረው ይሆን የሚለው ጥያቄ ግን ብዙ አሳሰበኝ ነበረ፡፡

እናቴ፣ እህቶቼና ወንድሞቼ ፣እንዲሁም ጠቅላላ ቤተ ዘመድ የየግል ስሜቱን ይግለጥ ቢባል በየራሱ አንድ አንድ ትልቅ መጽሐፍ ይወጣዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡ የሁሉም ሰው አንድ ላይ ቢደረግ ደግሞ ብዙ ጥራዞች ይሆናሉ እንደ ማለት ነው፡፡ (ያኔ ሳስበው ለአንድ የቤተሰብ አባል አንድ መጽሐፍ ሒሣብ የገመትኩኝ ይመስለኛል፡፡ አሁን በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት አማካይነት እንደተገነዘብኩት ከሆነ ግን ምናልባት አንድ መጽሐፍም የማይበቃው ሰው ሊኖር የችላል፡፡) እኔም ዛሬ የማቀርብላችሁ ጽሑፍ ከትልቅ የሕይወት መጽሐፍ የተቆነጠረ ትውስታ ነው፡፡

በኅብረተሰባችን ውስጥ በሰፈነው የትሕትናና የአክብሮት መልካም ባህል መሠረት ክቡር አባቴን አለቃ አያሌው ታምሩን በዚህ ገባኤ ፊት "አንቱ"

እያልኩ መጥራት እንደሚገባኝ አምናለሁ:: ነገር ግን ይህ አጠራር ማለትም እንቱታው የፍቅሬን ጥልቀት፣ የልቤን ቅርበት የሚቀንስ፣ አባቴን አባት ሳይሆን ራቅ ያለ ዘመድ የሚያስመስል ስሜት የሚፈጥር ስለሆነብኝ አልተመቸኝም። ስለዚህ "አንተ" እያልኩ መናገሬን ወገኖቼ በበጎ መልኩ እንዲያዩት በአክብሮት እጠይቃለሁ።

ትዝታዎቼ አባቴን በብዙ መልኩ ያሳዩኛል። አባትነቱ፣ እናትነቱ፣ ወንድምነቱ፣ እኅትነቱ፣ ጓደኝነቱ፣ መምህርነቱና የሃይማኖት መሪነቱ፣ ሌሎችም መገለጫዎቹ በየተራ ይታዩኛል። ከዚህም የተነሣ በሞቱ አንድ ሰው ብቻ ሳይሆን ، በጣም ብዙ የቅርብ ሰዎችን እንዳጣሁ ዓይነት ስሜት ይሰማኛል።

እንደ ንጋት ፀሐይ ብሩህና ምቹ የነበረው ውብ ገጽታው፣ የሰላም፣ የፍቅር፣የእውነት፣ የዕውቀት፣ የበረከትና የጽድቅ ቃላትን ብቻ ለማፍለቅ የታደለው መልካም አንደበቱና፣ ማራኪ ድምፁ ለትዝታዎቼ ማጀቢያ ይሆኑ ዘንድ ያለ ማቋረጥ በሕሊናዬ ውስጥ ይመላለሳሉ። በትዝታ ጉዞዬ ሄጄ ሄጄ የአባቴ የመጨረሻዋ የዕረፍቱ ሰዓት ላይ እደርሳለሁ። የሰላም፣ የደግነት፣ የመንፈሳዊነት ለዛ የፈሰሰበት፣ እንደ ንጹሕ ወርቅ ያምር የነበረው ብሩህ ፊቱም የትዝታዎቼ ሁሉ መነሻና መድረሻ ሆኖ ይሰማኛል።

እንደ አባት የሚታየኝ ገጽታው፤ ግርማ ሞገሱን፣ ጭምትነቱን፣ ጠንቃቃነቱን፣ ንቁነቱን፣ መካርነቱን፣ ቅንነቱን፣ ኩሩነቱን፣ ጀግንነቱን ያሳየኛል። በኩሩነቱና በጀግንነቱ ሥር የምመድበውን የአገር ፍቅር ስሜቱን ነገር በትንሹ ባወሳው ደስ ይለኛል።



አባቴን ከብዙ አቋሞቹ አንጻር ሳየው በደንብ የምረዳው ይመስለኛል። ስለ አገሩ ስለ ኢትዮጵያ ስላለው የነደደ ፍቅር ግን መረዳት እጅግ አድርጎ ይከብደኛል። ወጣቱ፣ አዛውንቱ፣ መነኩሴው፣ ቄሱ ሳይቀር የጠላትን፣ ቢችል ቢችል ወደ አሜሪካና አውሮፓ ባይችል የትም ጥሏት ለመሄድ የሚሳልባትን አገር አባቴ እንዴት እንዲህ ወደዳት? ለምን እንዲህ ወደዳት? እላለሁ። እንደ እናትና አባት ሁሉ አገርም አንድ ነችና። ልትወደድ፣ ልትከበር፣ ሊሰስትላት እንደሚገባ እምናለሁ። የአባቴ የአገር ፍቅር ስሜት ግን ከዚህ ሁሉ በላይ ነው።

በወታደራዊው መንግሥት ዘመን "ኢትዮጵያ" የሚለውን ቃል ሰሰማ በዚህ ስም ከለላነት በኢትዮጵያውያን ላይ የተፈጸመው ግፍ ነበር ቀድሞ የሚታየኝ። በኋላ ደግሞ "የብዙ ሺ ዘመናት ታሪክ ባለቤት፣ የሰው ዘር ምንጭና መገኛ፣ የኀያላን ነገሥታት፣ የሊቃውንትና የጀግኖች እናት ጥንታዊት አገር ኢትዮጵያ ናት"፤ የሚለው ትምህርትና ታሪክ በድንገት ተረስቶ፤ "ኢትዮጵያ የመቶ ዓመት ወጣት ነች፤" የሚል ትምህርት ሲመጣ ሁሉም እየገረመኝ፣ የአባቴም የአገር ፍቅር ስሜት ከሁሉ አልገጥም እያለኝ፤ "አባክህ አባቴ ራስህን እንዲህ አትጉዳ፤" ብዬ ሸቅብ ለመምከር የሞከርኩበት ጊዜ ሁሉ ነበረ። መጽሐፍ ቅዱስንና የታሪክ መጻሕፍትን እያጣቀሰ ከፍጥረተ ዓለም ጀምሮ እስከ ዛሬ ስለ ዘለቀው የኢትዮጵያ ምንነት፣ ማንነት ተንትኖ ያስረዳኛል። ትውልዱ የአገሩን ታሪክ በቅጡ የሚያስተምረው አጥቶ፣ ከፋና ደጉ ወሬ ተደበላልቆበት መላ እንዳላጣው ሲመለከት ደግሞ እጅግ ያዝናል።

ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ለኢትዮጵያውያን ስለ አገራቸው የተናገረውን፤ "እናንተ ዓይናሞቹ ማየት ያቃታችሁን እኔ ዕውሩ በዳሰሳ ላሳያችሁ!" እያለ ያስተማረውንም ብዙ ሰው ያስታውሰዋል ብዬ አስባለሁ። በአንድ ወቅት የአገር

ፍቅር ስሜት ምንድነው? ብዬ አባቴን ጠየቅሁት። "የአገር ፍቅር ስሜት ማለት አገርን በውበቷም በጉስቍልናዋም ጊዜ እኩል መውደድ ማለት ነው፤ የሰውን እናት ከመናፈቅ የራስን እናት መውደድ ማለት ነው። የአገር ፍቅር ስሜት ማለት ይህቺን በውበቷም በጉስቍልናዋም ጊዜ የራስ የሆነችውን አገር ከሙሉ ክብርና ነጻነት ጋር ጠብቆ፤ ቢቻል ይበልጥ አበልጽጎ፣ ባይቻል ደግሞ ያለውን ሳያጠፉ ለልጅ ልጅ ማስተላለፍ፣ ለትውልድ ማውረስ ነው፤" አለኝ።

የጊዜ ርዝመት ያስረጃቸው፣ የዘመን ምትሃት ያወየባቸው የሚመስሉ ኢትዮጵያዊ ቅርስና ውርሶችን ልብ ብዬ ለማየት በሞከርኩኝ ቁጥር አባቴ የነገረኝን ሁሉ በሙሉ ልቤ አመንኩኝ። ስለዚያች በመንፈስ እግዚአብሔር እየተመራ አባቴ ስለሚያያት፣ ስለሚወዳት አገሩ ስለ ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ጉስቍልና የተሰማውን ኀዘን የገለጠበትን አንድ አጭር ግጥም እስኪ ላቅርብላችሁ።

### ታላቋ ኢትዮጵያ

ታላቋ ኢትዮጵያ የአፍሪቃ ንግሥት፤
የካምና የኩሽ ሰንዱ እመቤት፣
ሉልና በትረ ወርቅ የማይለያት፣
የአቢስ፣ የሳባ፣ የናምሩድ እናት።
አንቺ ነሽ ኢትዮጵያ አንቺ ብቻ ነሽ፣
በዘውድ ማጌጥን ለዓለም ያስተማርሽ፣
ትናንትና በዘውድ በላንቃ ካባሽ፣
ከዓለም መንግሥታት ግንባር የነበርሽ፣
ዛሬ በኮፍያ በሸሚዝ ሆንሽ።



ያ ሁሉ የጥንቱ ጠፋና ክብርሽ፣
ውይዝርናው ቀርቶ ስለ ተጋለጥሽ።
ከወጣቶች ጋራ ዓለምሽን ልትቀጪ፤
ከነአሜሪካ ጋር ዓለምሽን ልትቀጪ፤
ብጥስጥስ ቅንጥስጥስ እያልሽ ብትመጪ።
ያወቀ፣ የሚያውቅሽ እጅግ ተጨንቀ፣
ያላወቀሽ ብቻ በሁኔታሽ ሣቀ።

በአባቴ የአባትነት ገጽታ ውስጥ ቅንነቱንና ንቁነቱን ታላቅ አርአያነት ያላቸው ሌሎች ገጽታዎቹን አሰባሰሁ። አባቴ የማንኛውንም ሁኔታ በጎ ገጽታ ማየት የሚያስቀድም፣ አገሩንና ወገኑን የሚወድ፣ የሰዎችን የሃይማኖትም ሆነ የፖለቲካ አመለካከት የሚያከብር የራሱ የሃይማኖትና የፖለቲካ አመለካከትም እንዲከበርለት የሚወድ፣ በነጻ ውይይት የሚያምን፣ አግባብነት ያለውን የሥልጣኔ ውጤት የሚያከብር፣ ስለ እያንዳንዱ ዕለታዊ የዓለምና የአገር ጉዳይ የሚነገር፣ የሚጻፍ ዜና የሚከታተል ንቁና ልበ ሙሉ ሰው ነበረ። በሃይማኖትም ሆነ በታሪክ፣ በፖለቲካም አንጻር ቢሆን ከማንም ሰው ጋር፣ ትንሽ ልጅም ቢሆን እንኳ፣ ከሁሉም ጋር እንደ ዐቅምና ችሎታው መወያየት የሚወድ ሰው ነበረ።

እንደ እናት የሚታየኝ ገጽታው በርኅራኄ፣ በደግነት፣ ቸርነት፣ ወደርና ልክ ማይገኝለት ፍቅር የተሞላ ነው።

እንደ አጎት የሚታየኝ ገጽታው ተግባቢነቱን፣ ቅርበቱን፣ ሣቁን፣ ቀልዱን፣ ምቹ መንፈሱን፣ የሕፃናት ያህል የጸዳ ቅን ልቡን ያሳየኛል።

እንደ ወንድም በሚታየኝ ገጽታው ውስጥ ደግሞ መከታነቱና አለኝታነቱ ጉልህ ሆኖ ይታያል።

እንደ ጓደኛ የሚታየኝ ገጽታው፤ የራሴን ያህል የማምነውን፥ ምንም ነገር የማልደብቀውን፥ በዓለም ላይ ከማውቃቸው ሰዎች ሁሉ እጅግ በጣም ውስጤን የሚረዳልኝን፤ የአባት ወዳጅ፥ የአባት ጓደኛ ያሳየኛል።

እንደ መምህር የሚታየኝ ገጽታው፤ ለሥጋዊና ለመንፈሳዊ ሕይወቴ የሚያስፈልገኝን ዕውቀት ሁሉ እንዳይጎድልብኝ ለማድረግ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል የመከረኝን፥ የደገፈኝንና ያስተማረኝን የአባቴን ውለታ ያስታውሰኛል።

በሃይማኖት አባትነት የሚታየኝ ገጽታው ጋ ስደርስ፤ አባትነቱ የእኔ ብቻ አለመሆኑ ይሰማኛል። የኢትዮጵያውያን ሁሉ አባት ነውና። እናም እዚህኛው ገጽታው ጋር ስደርስ በግሌ ለእኔ ለልጁ ያወረሰኝን ነገር ብቻ ነጥዬ ለማሳየት እሞክራለሁ።

በሃይማኖት አባትነቱ፥ በሐዋርያዊ ተልእኮው፥ በመንፈሳዊ ተጋድሎው ስለ ቤተ ክርስቲያን የተሸከመው መከራ መስቀል፥ የከፈለው መሥዋዕትነት፥ ያገኘው የመጨረሻ ክብር፥ ክብሬ፥ ኩራቴና ትምክሕቴ ነው። ከልጅነቴ ጀምሮ እያየሁ ያደግሁት ግለሰባዊ መንፈሳዊ ሕይወቱ ደግሞ፤ ሰንዱ እመቤት፥ ፅኑፍ ድርብ እናት፥ ፍኖተ ሕይወት እያለ የሚያሞግሳት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ምን ያህል የተቀደሰ እንደ ሆነ ለማመን ተጨባጭ ማስረጃ ሆኖኛል። ከዚህ በተጨማሪም ስለ ሃይማኖቴ ማወቅ የሚገባኝን ሁሉ አብጠርጥሮ፥ እንጠርጥሮ አስተምሮኛል። ሁሉን ቻይ የሆነውን አምላክ እግዚአብሔርንም በሃይማኖት እንዳየው ረድቶኛል።



በመጨረሻ የሰንብቱ ቀናቶችና በሞቱም የክብር ክብር የምታሰጥ ቅድስት ሃይማኖት እንዳለችኝ፥ ብዙዎች የተሰናከሉባትን፥ እንደ ዋዛ፥ እንደ ቀልድ ያዩአትን የእመቤታችንን የቅድስት ድንግል ማርያምን አማላጅነት፥ ክብርና ቅድስና በማያወላውል መንገድ አጽንቶልኛል።

ስለዚህ ታላቅ ውለታው የሃይማኖት አባቴን፥ የሃይማኖት መሪዬን አመሰግነዋለሁ። የቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ የንስሐ ልጅ መምህሩን ባመሰገነበት ምስጋና እኔም አባቴን፥ መምህሬን፤ «እምቅድመ ሞትከ መምህርየ አንተ፤ ወእምድኅረ ሞትከ መምህርየ አንተ» «በሕይወት ዘመንህ፥ ከሞትክም በኋላ መምህሬ አንተ ነህ» እያልኩኝ በዚህ ጉባኤ ፊት አመሰግነዋለሁ። ለዚሁ ስሜቴ መግለጫነትም በፅረፍቱ ዕለት የቋጠርኳትን አጭር ግጥም እነባለሁ።

እያሌው ታምሩ ዐምደ ሃይማኖቴ
አጥንቴ፥ ሥጋ፥ ደሜ፥ ማተቤ፥ ኩራቴ
በሥጋ በመንፈስ ወለደኝ ሁለቴ።

የተከበራችሁ ወገኖቼ!

አንድ ትውስታ ልጨምር፤ ይኸውም የአባቴ አመጋገብ ነው። አብዛኛውን ጊዜ በጾም የተወሰነው፥ ፍስክም ሲሆን ባተወሰኑ ጉርሻዎች የተመጠነው አመጋገቡን ላየ ሰው ሰማንያ አራት ዓመት ዕድሜ መቈየቱ ተዓምር ይሆንበታል። "ሰው በእግዚአብሔር ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም።" ተብሎ የተጻፈው ቃለ እግዚአብሔር የታመነ በመሆኑን በአባቴ ሕይወት ተግባራዊ ሆኖ አይቼዋለሁ።

በንግግሬ መግቢያ ላይ እንደ ገለጽኩት ስፊውን የትዝታ ባሕር በፍጹም አልነካሁትም ለማለት እችላለሁ። ሆንም ትንሽ መሞከር አይከፋም ብዬ የመሰሰኝን አቅርቤላችኋለሁ። በትዕግሥት ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

አባቴንም ላመስግነው። ደግ አባቴ! ስለ አንተ ያሉኝን ትዝታዎች ሁሉ፥ ታሪክህን ሁሉ በጽሑፍ አስፍሬ ለወገኖቼ ለማሳወቅ ብችል ምንኛ ደስ ባለኝ! ባገኘሽው አጋጣሚ ሁሉ፤ "እናንተ ዐይናሞቹ ማየት ያቃታችሁን የአገራችሁን ማንነት፥ የሃይማኖታችሁን ቅድስና እኔ ዕውሩ በዳሰሳ እየመራሁ ላሳያችሁ!" እያልክ የሙሀከው ጩኸት ተሰምቶ፥ ፍሬ አፍርቶ ባይ ምንኛ ደስ ባለኝ።

በጸሎት ክፍልህ ውስጥ ጭብጥ፥ ክርምት ያልከላቸው፥ ቀንና ሌሊት ያስቀስከላቸው ውዷቱ አገር ኢትዮጵያ፥ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንና ወገኖችህ ኢትዮጵያውያን ዛሬም ጸሎትህ ያስፈልጋቸዋል። ይህን ስነግርህ የከበረች ነፍስህ እንደምትሰማኝ በማመን ነው።

አባቴ! ሕይወትህ ትምህርት ቤቴ፥ ተግባርህ ጽናቴ፥ ትዝታህ የዘለዓለም ስንቄ፥ ሃይማኖትህና አገርህም ካንተ የወረስኳቸው ሀብቶቼ ናቸው። የዚህ ሁሉ ሀብት ባለቤት ስላደረግኸኝ እወድሃለሁ! አመሰግንሃለሁ።

ሁሉን ቻይ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ! ክብር ተመስገን!

ሥምረት አያሌው ታምሩ



## መግቢያ

አባቴ "የአፍሪካ ንግሥት" እያለ የሚያወድሳትን አገሩን ኢትዮጵያንና "ስንዱ እመቤት" እያለ የሚያሞግሳትን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት የነበረውን እምነት ለወገኖቹ ለማሳወቅ ከ፶ እስከ ፰ ዓመታት ያህል አስተምሯል፡፡ በትምህርቱም የኢትዮጵያዊነትን ቅርስና ውርስ ጥለው ከዋና ግንዳቸው ተገንጥለው ሲባዝኑ ከነበሩ ኢትዮጵያውያን ብዙዎችን ወደ ማንነታቸው እንዲመለሱና ከግንዳቸው እንዲጣበቁ ረድቷል፡፡ አገሩን፣ ወገኑንና ሃይማኖቱን አክባሪና ወዳጅ ሰው እንደነበረ የሚያጠራጥር ነገር ይኖራል ብዬ ባላስብም እጅግ ጥልቅ ስለነበረውና በሃይማኖት ዓይን ብቻ ሊታይ ስለሚችለው የእምነቱ ምጥቀት ግን ብዙዎችሙሉ ግንዛቤ አላቸው ብዬ አላምንም፡፡

በመሆኑም በቅርበት ስላየሁትና ስለተገነዘብኩት የአባቴ መንፈሳዊ ህይወትና እምነት ለመመስከር ያስችለኝ ዘንድ "አባቴና እምነቱ" የተሰኘውን ይህን መጽሐፍ ጻፍኩኝ፡፡ የአባቴን ታሪክ ለመጻፍ መሞከር ዓባይን በጭልፋ እንደሚባለው ዓይነት ቢሆንብኝም በተለይ ለእኔ ልዩ ትርጉም የሚሰጠኝን የመንፈሳዊ ሕይወቱን ገጽታ በመመስከር ረገድ ግን በጥቂቱም ቢሆን ኃላፊነቴን የተወጣሁ ይመስለኛል፡፡

ከልጅነት እስከ ዕውቀት በተጓዝኩበት የዕድሜ መንገድ፤ ስለ አባቴ ሕይወት በቅርበት የተገነዘብኩት ሁሉ በቸልታ ላልፈው የማልችለው ብዙ ቁምነገር ያለበት ነው፡፡ ችላ ለማለት ብፈልግም የሕሊና ዕረፍት እየነሳ የሚቀሰቅሰኝ ብዙ ጉዳይ አለ፡፡ በውስጡም ከጥንተ ፍጥረት ጀምሮ በእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ የነበሩና ያሉ ኢትዮጵያውያን ዋነኛ ባለጉዳዮች ናቸው፡፡

እርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በእምነታቸው ጸንተው ላገለገሉ ሁሉ የክብር ክብር የምታሰጥ ደገኛ ሃይማኖት ስለመሆኗ በቀደሙ ቅዱሳን ሕይወት ውስጥ ብዙ መስክርነት የምናገኝ ቢሆን፤ በዘመናችንም ይህ ጸጋ እንዳልተቋረጠባት ለማስመስከር ከሚበቁ መንፈሳዊ ታሪኮች አንዱ የአባቴ የሕይወት ታሪክ እንደሆነ አምናለሁ፡፡ የእምነትን ነገር በጥልቀት ያላዩና ያልተገነዘቡ፣ ምናልባት ቢገነዘቡም በተለያየ ምክንያት ትኩረት ያልሰጡ ሁሉ ስለ ሃይማኖታቸውና ስለ ቤተ ክርስቲያናቸው ካላቸው ውሱን ግንዛቤ በተጨማሪ በአባቴ ሕይወት ምክንያት የሚያተርፉት ጥቂት ዕውቀት ሊኖር ይችል ይሆናል የሚል ተስፋ አለኝ፡፡

አባቴ ኑሮውን በአዲስ አበባ ከተማ አድርጐ ሐዋርያዊ ተልእኮውን መወጣት ከጀመረበት ከ፲፱፻፴፱ ዓ.ም.ጀምሮ እስከ ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. ድረስ በነበሩት ፷ ዓመታት ከፍተኛ የሆነ የማስተማር ሥራና በመጨረሻም "ሰማዕት በእንበለ ደም" ያሰኘውን ከፍተኛ ተጋድሎ ፈጽሟል፡፡ የተጠራበትን ሐዋርያዊ ተግባር ሲከውን ዋነኛ እምነቱ የነበረው እግዚአብሔር የሚከብርበትን ሥራ ብቻ ሠርቶ ማለፍ ነበረ፡፡ "ሰው ምን ይለኛል" ከማለት ይልቅ "እግዚአብሔር ምን ይለኛል" ማለትን ዋነኛ የሕይወቱ መመሪያ አድርጎ የኖረ እነደመሆኑ መጠን አንድ ብቻውን የቆመ አስኪመስል ድረስ ላመነበት ዓላማ እስከ መጨረሻው ተሟግቷል፡፡ በዚህ ረገድ በአባቴና በቤተክርስቲያን ባለሥልጣኖች መካከል የተፈጠረው ሁሉ አልፎ አልፎ ሲነገር እንደሚሰማው በግለሰቦች መካከል የተካሄደ ትግል አለመሆኑን መገንዘብ ጠቃሚ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ አባቴ የፈጸመው ሁሉ ስለ ቤተክርስቲያን ክብር የተደረገ መሁኑንና በአባቴ ላይ የተፈጸመውም በቤተክርስቲያን ላይ የተፈጸመ መሆኑን በግልጽ ለማየት



ለሚረዳ ነው፡፡ የአባቴ ፀብ ከግለሰቦች ጋር አልነበረም፡፡ ስለ ግል ጥቅም ወይም ዝና የተደረገም አልነበረም፡፡ ስለ ቤተክርስቲያን እንጂ፡፡ አባቴ ቤተ ክርስቲያንን ይጠብቁ ዘንድ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሁሉ በቤተክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ እውነትንና እውነትን ብቻ ለማስፈን ሲባል መያየት እለባቸው የሚል እምነት ነበረው፡፡ ይህን በተመለከተ ስለነበረው አመለካከት የሚከተለውን ብሎ ነበር፡፡

"በመኃልየ ማኅልይ ሰሎሞን በመጀመሪያው ምእራፍ ላይ "ደቂቀ እምየ ተበአሱ በእንቲአየ፥የእናቴ ልጆች ስለ እኔ ተጣሉ፡፡ ተከራከሩ፡፡" "እንበሩኒ ዐቃቤተ አጸደ ወይን፥ የወይን ጠባቂ አድርገው ለይመውኝ ነበር፤" ግን "አጸደ ወይን ዘዚአየ ኢዐቀብኩ፥ የተሰጠኝን ወይን አልጠበቅሁምና በዚህ ምክንያት የእናቴ ልጆች ተጣሉ፡፡" የሚል ተጽፏል፡፡ እንግዲህ የቤተክርስቲያን ልጆች ጸብ የሚፈጥሩት፤ ክርክር የሚያደርጉ በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ላይ የተሾሙ ጳጳሳት፣ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ቀሳውስትና ሌሎችም መሪዎች እንዲሁም ደግሞ መምህራን እነዚህ በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ላይ በአስተዳደሩ፤ በትምህርቱ፣ በሥርዓቱ፣ በእምነቱ አንዳንድ ጉድለት ሲያመጡ ሌሎች ደግሞ ይቃወማሉ ይከራከራሉ፡፡ ሕግ ነው ማለት ነው፡፡ "ስለ እኔ ተጣሉ"ይላልና፡፡[1]በዚህ እምነቱ የተነሳ ስለቤተክረስቲያን ተልዕኮ ሲል የግምባር ሥጋ ሆኖ ሲንገላታ ኖሯል፡፡

"የሃይማኖት አስተማሪ የሆነ ሰው በመንገዱ ላይ ፖለቲካ የሚባል እንቅፋት ሊደቀንበት አየገባም" የሚል እምነት የነበረው አባቴ ለሐዋርያዊ ተልእኮ

[1] መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን፡ምዕራፍ ፩፡፭፡፡

ከተሰማራበት ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ሩጫውን ጨርሶ እስካረፈበት የኢሕዴግ ዘመነ መንግሥት ድረስ ባደረገው ሐዋርያዊ ጉዞ ወቅት ያጋጠሙትን የየመንግሥታቱ ፖለቲካ ጠባዮች በቤተ ክርስቲያን ነጻነት ላይ ያስከተሉትን ተጽዕኖና ችግር በተመለከተ በማስተማር፣ በመምከር፣ በመተቸትና በመገሰጽ ረገድ እጅግ ጠቃሚነት ያላቸው፣ በምሳሌነታቸውም ተጠቃሽ ሆነው ሲታወሱ የሚኖሩ ከፍተኛ ተግባራትን ፈጽሟል፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በእግዚአብሔር፣ በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ፊት የገቡትን ቃል ኪዳን በመዘንጋት ከቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ውጪ መሰማራታቸው አግባብነት እንደሌለው አስተምሯል፤ መክሯል፤ ተቃውሞውን አሰምቷል፡፡ በተለይም በቤተ ክርስቲያን ስም የተሰጣቸውን ክብር፣ ሞገስና ሥልጣን መሣሪያ በማድረግ እቢያው ከጉያዋ ውስጥ ተቀምጠው በይፋ ቀኖናዋንና ሥርዓቷን ደፍረው ለማስደፈር የሠሩ ሹማምንትን ከቤተ ክርስቲያንና ከምእመናንን ለመለየት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አውግዟል፡፡

ከባዕዳን ይልቅ በራሷ ልጆች፣ከውጪ ኃይላት ይልቅ በውስጥ አዋቂዎች እየተቦረቦረችና እየተመዘበረች ያለችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ከማንኛውም ጉዳት መጠበቅ የምእመናን ተግባር መሆን እንዳለበት ያምን የነበረው አባቴ በዚህ ረገድ ምእመናን ቤተ ክርስቲያናቸውን ተጠንቅቀው እንዲጠብቁ በተደጋጋሚ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ከሕገ እግዚአብሔር አፈንግጠው ጸጋ እግዚአብሔርን በገዛ ራሳቸው ያጡ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ከበው የሚያጨበጭቡ ምእመናንንም ከማጨብጨብ ይልቅ በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያን የተቋቋሙ የሰበካ ጉባዔ መዋቅሮችን በመጠቀም ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅሙ ሰዎችን መምረጥ እንዳለባቸው



ደጋግሞ መክሯል፡፡ በአሥራትና በበኩራት ስም ራሱ በእጁ ወስዶ በሚሰጠው ገንዘብ አማካይነት ትከሻቸውን አሳብጠው ከገዛ ቤተክርስቲያኑ የመንፈስ ሰደተኛ የሚያደርጉትን ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ቀኖናና ሥርዓት ብቻ እንዲገዙ በማድረግ ሥልጣነ ክህነታቸውን ለምእመናን ግልጋሎትና ለእግዚአብሔር ክብር ብቻ እንዲያውሉት ማስደረግ እንዳለበትም አስተምሯል፡፡ ይህ የማይሆን ከሆነ ግን የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ሀልውና እስኳል የሆነውን የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ ልዕልናና ሀልውና አስጠብቆ መኖር እንደማይቻል ደጋግሞ አስጠንቅቋል፡፡

በመጨረሻም ቀደምት ቅዱሳን አባቶቹ ከደረሱበት መንፈሳዊ ብቃት ላይ ደርሶ እንደነበረ በሚያመለክቱ የክብር መገለጫዎች ተከቦ፣ እጅግ ይወዳትና ያከብራት በነበረችው በጸመ ፍልሰታ በአስራ አራተኛ ቀን ከዚህ ከሚጠፋው ዓለም ወደማይጠፋው ዓለም ተሸጋግሯል፡፡ የቀብር ሥነ ሥርዓቱም እጅግ ብዛት ያለው ህዝብ በተገኘበት በደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በሦኛዪቱ መልእክቱ በቁጥር ፲፩ እና ፲፪ ላይ ስለ ተወደደ አገልጋይ ድሜጥሮስ ሲጽፍ «... ለድሜጥሮስ ሁሉ ይመሰክሩለታል፤ እውነት ራስዋ ትመሰክርለታለች፤ እኛም ደግሞ እንመሰክርለታለን» እንዳለ "እውነት" እውነተኛ ቦታዋን ስትይዝ ቤተክርስቲያን ራሷ በይፋ ለአባቴ እንደምትመሰክርለት እምነቴ የጸና ነው፡፡ ለአሁኑ ግን የእኔን ምስክርነት ለትውልድ ለማስተላለፍ ያህል የተቻለኝን ሞክሬአለሁ፡፡

ሥምረት አያሌው ታምሩ

# ምእራፍ ፩

## የልጅነት ሕይወት
## ፲፱፻፲፭ - ፲፱፻፳፫

# ልደትና የሕጻንነት ዓመታት

አባቴ አለቃ አያሌው ታምሩ የተወለደው መጋቢት ፳፫ ቀን ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት ነው፡፡ የልደቱን ቀን ያወቀው እናቱ ወይዘሮ አሞኘሽ አምባዬ ከነገሩት ምልክት በመነሳት ነው፡፡

"እታታ" በሚል የቁልምጫ ስም እናቱን ይጠራ የነበረው አባቴ፤ ከዕለታት በአንዱ ቀን፤

"እታታ፣መቼ ነው የተወለድኩት? ዘመኑ ትዝ ይልሽ ይሆን?" ብሎ ጠየቃቸው፡፡እሳቸውም፤

"የጐንደርና የበጌምድር ገዢ የነበሩት የንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ አጽም ከጐንደር ወደ ሸዋ በፈለሰበት ዘመን ነው፡፡ የንጉሡን አጽም ያጀበው ሠራዊት ያለፈው በእኛ ሠፈር በኩል ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ በተፈጸመበት ዓመት ነው የተወለድከው፡፡ትዝ ይለኛል፡፡ ቀኑ መጋቢት ጊዮርጊስና ሆሳዕና ተደራርበው የዋሉበት ሰንበት፣ ሰዓቱም እኩለ ቀን ላይ ነበር፡፡" ብለው መለሱለት፡፡

ወይዘሮ አሞኘሽ የነገሩትን መሠረት አድርጎ በባህረ ሀሳብ ጥበብ[1] ሲያሰላው ትክክለኛውን የትውልድ ዘመኑን አወቀው፡፡ በዚሁ መሠረት "የተወለድኩት በ ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት መጋቢት ፳፫ ቀን በዕለተ ሆሣዕና ነው፡፡" ብሎ ነገረን፡፡

[1] የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ቅርስ በሆነው በባሕረ ሀሳብ አቆጣጠር መሠረት የአባቴ የልደት ቀን በሌት እንደሚከተለው ነው። በፀሐይ አቆጣጠር በ፲፱፻፲፰ ዓመተ ዓለም ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት ፣ ከዓመተ ዓለም ጀምሮ ሲቆጠር ደግሞ በ፯ሺ፬፻፲፰ ዓመት ፣ በጨረቃ አቆጣጠር ፯ሺ፬፻፲፰ ዓመት በ፯ ወር በ፲፱ ቀን በ... ሰዓት በ፯ ጥንተ ዮን ማለትም መጠቀሚያ ፩ ቀን ... ዕለት በተተከለ በ፱ ወንበር፤ በ፲፱ አበቅቴ፤ በ፲ መጥቅዕ፤ በ፲፩ ሠርቀ ሌሊት፤ የሚያዝዩ ጨረቃ ሠርቅ ባደረገች ፲፮ኛው ቀን ነው። ይኸውም በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር በ፯ኛው ወር፤ በዕብራውያን አቆጣጠር በ፲፱ኛው ወር፤ በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ፫ኛው ወር፤ በሐሳብ ዐረብ በ፱ኛው ወር ሚጠተ ብርሃናት[1] ሲሆን ጥቂት ቀን ሲቀር፤ ፀሐይ አልፈጸመል[1] በሚባል ኮከብ አዳራሽ እያለች፤ በ፳ ሠርቀ ዕለት[1] ማለትም ዕሁድ ቀን በመጋቢት ፳፫ በዕለተ ሆሣዕና ፣ ሆሣዕና በአንድ ዓመት ቀመር መጋቢት ፳፫ ቀን ፳፯ ጊዜ በሚውልበት ነው።



አባቴ ስለተወለደበት ዕለት ልዩ ስሜት የነበረው ይመስላል፡፡ ይህንንም ፣ የልጅነት፣ የወጣትነትና የጎልማሳነት ዘመናትን እልፍ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ ሰብሳቢ በነበረበት ዘመን በውጭ አገር ከሚኖሩ ተማሪዎቹ አንዱ ለነበረ ኢትዮጵያዊ በጻፈው ደብዳቤ ላይ፣

" የተወለድኩት በ ፲፱፻፲፰ ዓመተ ምሕረት መጋቢት ፳፫ ቀን በዕለተ ሆሣዕና ነው፡፡ የሕይወቴ ፍሬ እንግዲህ የዚህ ዕለት ውጤት ነው ልል እችላለሁ፡፡ ሊቃውንቱ ዝም ባሉበት፥ ሕፃናት በምስጋና አንደበታቸውን በፈቱበት፥ ድንጋዮች እንዲናገሩ በታዘዙበት በዚያ ቀን መወለዴ የሕይወቴ መምሪያ የሆነ ይመስለኛል፡፡" በማለት መዋዕለ ሕይወቱንና የልደቱን ቀን ከዕለተ ሆሣዕና ጋር በማነጻጸር ገልጦለታል፡፡

ለአባቱ ሁለተኛ፥ ለእናቱ የበኵር ልጅ የሆነው አባቴ የተወለደው በጥንቱ የጎጃም ጠቅላይ ግዛት፣ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ፤ ልዩ ስሙ ቤተ ንጉሥ በተባለ ሥፍራ፤ በአያቱ በወይዘሮ አማሁሽ ከበበው ቤት ነው፡፡

እናቱ ወይዘሮ አሞኘሽ አምባዬ፥ አባቱ አቶ ታምሩ የተመኝ ይባላሉ፡፡ እንደማንኛውም የጎጃም ተወላጅ ሁሉ ወይዘሮ አሞኘሽና አቶ ታምሩ ወደ ኋላ ቆጥረው የሚያስመሰክሩት የባለ አገርነትና የባለአባትነት የዘር ሀረግ የነበራቸው የጐጃም ነጋሽ ወገኖች ናቸው፡፡

የኖኅ ልጆች ምድርን በሰጣ ተካፍለው ኑሮን እንደገና ሲጀምሩ አንዱ የአንዱን ርስት ለመቀማት እንዳይከጅልና ሰላም እንዳይጠፋ በማሰብ ኖኅ ጥብቅ መሐላ አድርጓል፡፡ ይህን ልተላለፍ የሚለውንም ረግሟል፡፡ በዚሁ ምክንያት በጎጃም የተወለደ ሁሉ በሰላምም ሆነ በጦርነት የመጡበትን ሁሉ እንደ ሁኔታው አካፍሎ ወይም አስጠግቶ ከአያት ቅድመ አያት በወረደለት ርስቱ ተወስኖ ከመኖር ውጪ የሌሎችን የመጋፋት ጠባይ አልነበረውም፡፡[2] በዚሁ ምክንያት በወታደራዊው

[2] አለቃ ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ የጐጃም ትውልድ በሙሉ ከአባይ እስከ አባይ ገርማ ጌታሁን እንዳዘጋጀው፣ ፳፻፫ ዓ.ም.

መንግሥት ዘመን በመሬት ላራሹ ሰበብ የባለአባትነትና[3] የባለርስትነት መብቱን እስኪገፈፍ ድረስ የዘር ሐረጉን ቆጥሮና አስመስክሮ የአባቴ፣ የእናቴ የሚለው አጽመ ርስት የሌለው ጉጃሜ አይገኝም ነበር።

የአባቴ ወላጆች ማንነትም ከ፲፪ቱ ነገደ ጉጃም አባቶች መካከል ከሆኑት ከእነማይ፣ ከእነሴ፣ ከጎዛምን፣ ከአነደድ፣ ከጥላትግን፣ ከአዋበልና ከውድሚት በሚወርዱ ሐረገ ትውልዶች የተገመደ ነው። ባስአገሩ "ዋርያ ዋዮን" እያለ ከሚጠራው ከጃራው፣ ከዲማና ከደብረ ጽሙና ከሚመጡ ሐረገ ትውልዶች የተገኙት ተዋበች ዋሴ፣ የከኛ፣ የደብረ ወርቅና የዲማ ባለአባት የሆኑትን የተመኙ ጃግናን አግብተው ሁለት ሴቶችና አራት ወንዶች ልጆችን ወልደዋል። ከአራቱ ወንዶች ልጆች አንዱ የአባቴ አባት አቶ ታምሩ የተመኝ ናቸው።

ከለምጨን፣ ከፈንጠርጌና ከዲማ ባላባቶች የሚወለዱት አሊጋሽ ከበበውና ከሸበል በረንታ፣ ከደጌንና (ከደጀንና) ከጉባያ የሚወለዱት አምባዬ ካሣ ደጣሞ የአባቴን እናት እሞኘሽ አምባዬን ይወልዳሉ።

ወይዘሮ እሞኘሽ አምባዬና አቶ ታምሩ የተመኝ ከተጋቡ ጀምሮ ይኖሩ የነበረው የተዋበች ዋሴ ርስተ ጉልት በነበረው በእናርጅ ወረዳ ልዩ ስሙ "ጥሬ በደጅ" በተሰኘ ቦታ ላይ ነበር።[4] የአባቴ ወላጆች አመጣጣቸው ከአራሽ ቤተሰቦች በመሆኑ አልተማሩም። መተዳደሪያቸውም እርሻንና ንግድን የቀላቀለ ነበር።

---

[3] በአሁኑ ዘመን "ባለርስት"፣"ባለአባት"፣ "አጽመ ርስት" የተባሉት ቃላት የጨለቁና የተጠለፉ መገባበ ቃላት ወሰዋ የነበ በመሆናቸው የቀደሙ ትርጉማቸው እየተረሳ መምጣቱ እባቱ እንደአስተማረኝ ግን ጥንታዊ ትርጉማቸው ከዚህ የሚከተለው ነው።

ባለአባት፣ የተሰኘው ቃል በባለ ርስት ወይም በባለ ምድር ከሚለው የሚገባ ቃል ይወጣል። ትርጓሜው ባለርስት፣ባለቤት፣ ቀደሞ ማለት ነው። እንደ አባቴ እምነት ኢትዮጵያዊ ሁሉ ባለአባት ወይም ባለአገር ተብሎ ይጠራ ዘንድ ተገቢ ነው። "ዜጋ" ተብሎ መጠራት የለበትም። "ዜጋ" ማለት ትርጉሙ ተገዢ ጭሰኛ ማለት ነው። እንደም ከሌላ አገር በአንግድነት የሰፈረ እንጂራ ፍለጋ የመጣ ወይም ለጊዜአዊ ኑሮ የመጣ የኢትዮጵያ አጽመ ርስት የሌለው ማለት ነው። በዚህ የተነሳ ኢትዮጵያውያንን ለማመልከት ሲነገር "ባለአገር" እንጂ "ዜጋ" መባል አይገባውም ይል ነበረ። እኔም እንደ አባቴ እምነት ባለ ርስትነቱና ባለ አባትነቱን ለማሳወቅ ሰፊ ሥርወ ዘሩን ጠቅሶ ጽሬአለሁ። "ባለርስት"፣"ባለአባት"፣ "አጽመ ርስት" እያልኩኝ በመቀጠል ሁሉ ለማለት የፈለገሁት ከጥንታዊው የቃሉ ትርጉም አንጻር መሆኑን ለመግለጥ እወዳለሁ።

[4] ጥሬ በደጅ ተብሎ የተሰየመው ቦታ ስሙን ያገኘው ከአፈሩ ለምነት የተነሣ ሲሆን እንዲን በጣም የተበላሸ፣ በደጃፍና በዋር የተበተነውና የተተከለው ሳይቀር በቀላሉ የሚበቅልበት ለምነት ቦታ እንደ ነበር ይነገራል።



ወይዘሮ እሞኘሽ እርግዝናቸው እየገፋ ሄዶ የሚወልዱበት ወር ሲገባ በጥንታዊው የኢትዮጵያውያን ወይዛዝርት ሥርዓት መሠረት ከጥሬ በደጅ ወደ እናታቸው መኖሪያ ወደ ቤተ ንጉሥ ሄዱ። በዚያም አባቴን ወለዱ። በዐርባኛው ቀንም በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም ስመ ጥምቀቱ ወልደ ጊዮርጊስ ተብሎ ክርስትና ተነሣ።

ወይዘሮ እሞኘሽ አምባዬ ልጃቸውን ክርስትና አስነሥተው ከጠነከሩ በኋላ ወደ ባለቤታቸው መመለስ ቢኖርባቸውም ሳይመለሱ ቀሩ። ያለመመለሳቸው ምክንያት በእርሳቸውና በባለቤታቸው መካከል የተፈጠረ ጊዜያዊ ግጭት ነበር። አለመግባባቱ ከእነርሱ አልፎ ወደ ቤተሰብ በተለይም ወደ እናቶቻቸው በመሸጋገሩ ምክንያት በቀላሉ መብረድ የሚችለው ነገር ከረረና ተፋቱ።

አባቴ በዚያው በተወለደበት በአያቱ በወይዘሮ አማሁሽ ከበበው ቤት እስከ ሦስት ዓመት ዕድሜው ቆየ። ከዚያ በኋላ ግን ወይዘሮ እሞኘሽ እምባዬ ሌላ ትዳር ያዙ። በዚያን ዘመን ማግባት፣ መፍታት እጅግም ክብዶ የማይታይ በተጨማሪ የዝምድና መፍጠሪያም ስለበረ ዩወገናቸውን ዝምድና ፈልገው ለመጡ ሰው ተዳሩ። አዲሱ አባወራ ይኖሩ የነበረበት ሥፍራ ገደብ ጊዮርጊስ የሚባል ሲሆን በእናርጅ ወረዳ ዓባይ አፋፍ ላይ ይገኝ ነበር። ወይዘሮ እሞኘሽ ወደ አዲሱ ትዳራቸው ሲሄዱ አባቴን ይዘውት ነበር።

እኒሁቹ ሙሽሮች ኑሮን ተለማምደው ትዳራቸው ከተሟሟቀ በኋላ፣ የአርሶ አደሮች ሥራ ቀለል ባለበት አንድ ቀን አባወራው በጊዜ ወደ ቤታቸው ተመለሱ። ሰላምታ አቅርበው ወደቤት ውስጥ ዘለቁ። ሰዓቱ ወደ ምሽቱ ያደላ ስለነበረ ወይዘሮ እሞኘሽም እስከ እራት የሚያማሽ መቆያ ቆሎና ጠላ አቀረቡላቸው።

ከዚያም እንደ አገሩ ልማድ የዕለት ትኩስ እንጀራ ለማድረስ ተፍ ተፍ ማለት ጀመሩ። በዚህ ወቅት ልጃቸው ከደጃፍ ወደ ቤት፣ ከቤት ወደ ደጃፍ እየተሯሯጠ በመጫወት ላይ ነበር። እናቱ እንጀራ መጋገር

መጀመራቸውን ያስተዋለው ሕፃን ምባድ በባዱ ቁጥር ያስለመዱት ሙብጦ[5] ትዝ አለው፡፡ ቶሎ እንዲሰጡት ተቻኮለና፤

"እታታ፤ እንዲህ አድርገሽ ስጭኝ" እያለ ትኩስ እንጀራ ከመሶብ ቆርሶ በትንንሽ እጆቹ እየጨበጠ ለእናቱ አሳያቸው፡፡

ሕፃኑ ለእናቱ ያቀረበው ጥያቄ ከመደብ ቁጭ ብለው ሁኔታውን ለሚከታተሉት አባወራ ደስ ሳያሰኝ ቀረ፡፡ አበሳጫቸው፡፡ አበሳጭቶአቸውም አልቀረ ክፉ አናገራቸው፡፡

"ሂድ ወዲያ! አባትህ ያረሰው መሰለህ!"በማለት፤ ለልጅ የማይስነዘር ከባድ ነገር ከአንደበታቸው ወጣ፡፡ በዚህ አላበቁም እንጀራ የጨበጠውን እጁን መቱት፡፡ ሙብጦ በመጠበቅ ላይ የነበረው ሕፃን በደረሰበት ዱላ ስለ ተደናገጠ ይዞት የነበረውን የእንጀራ ቁራሽ ወርውሮ እያለቀሰ እናቱ እቅፍ ውስጥ ተሸጎጠ፡፡

የተፈጠረው ሁናቴ እናቲቱን አስከፋ፡፡ ክፉና ደግ የማያውቀው ሕፃን ላይ በተሠነዘረው ኃይለኛ ቃል ተቆጡ፡፡"የማንን አባት ማን ይሳደባል?" "እንዴት ለእንጀራ ብለህ ህፃን ልጅ እንዲህ ትናገራለህ? እንዴትስ ትመታዋለህ? በማለት ተናገሩ፡፡

በዚህን ጊዜ አባወራው የመጀመሪያው ሳያንስ ሁለተኛ ጥፋት ሠሩ፡፡ የተቆጡ ሚስታቸውን ሊማቱ ተነሡ፡፡ ወይዘሮ አሞኘሽ ግን ዱላውን በጸጋ ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ በሁኔታው ከመበሳጨታቸው የተነሳ የጣዱትን ምጣድም ሆነ ያሰፉትን እንጀራ እንኳ ዞር ብለው ሳያዩ ልጃቸውን አቅፈው ከቤታቸው ወጡ፡፡

---

[5] ሙብጦ እናቶች እንጀራ በሚጋግሩ ጊዜ ለልጆቻቸው የሚያዘጋጁት የምግብ ዓይነት ነው። ሙብጦ ለመጋገር ሲሰናዱ ከሞከው ሊጥ እርሾ ወስደው አዲስ ዱቄት ያሟሉ። ይህንን በኋ ከፈናተኛ ይሰታል። ከዚያም በሚጋግሩት እንጀራ ጣልቃ አስገብተው ወይም መጨረሻ ላይ ይጋግሩታል። ቤታቸው ውስጥ ያሉትን ዘይትም ይሁን ቅቤ ከበርበሬ ጋር አዋህደው ከጋገሩት አፍለኛ ጋር አሽተው ያዘጋጁታል።



ወደሚቀርባቸው ወደ አጎታቸው ወደ ፊታውራሪ ጥሩነህ ግሀሉ ቤት ሸሹ፡፡ ሆኖም ግን ባለቤታቸው ከኋላቸው ተከትለዋቸው ነበር፡፡ ይህንን የተገነዘቡት ወይዘሮ አሞኘሽ አጎታቸው መልሰው እንዳይሰጡአቸው በመሥጋት በገቡበት የጓሮ በር ተመልሰው ወጥተው ወደ እናታቸው አገር ወደ ቤተ ንጉሥ ሽሽታቸውን ቀጠሉ፡፡

## የፈንጣጣ ህመምና አደጋው

እናትና ልጁ ቤተ ንጉሥ የሄዱ ሰሞን ፈንጣጣ በአገሩ ገብቶ ነበር፡፡ ይኸው ፈንጣጣ የእማሁሽ ከበበውን የመጨረሻ ልጅ ያሳብ ደርሰህን ይዟት ደረሱ፡፡ በአካባቢው ፈንጣጣ መግባቱን ሳያውቁ ቤተሰቡን የተቀላቀሉት ወይዘሮ እሞኘሽ ሕፃኑ እንዳይታመምባቸው በመሥጋት ክትባት እንዲሰጠው አደረጉ፡፡ በዚሁ መሠረት ሦስት ጊዜ የተከተበ ቢሆንም ፈንጣጣው ሳይወጣለት ቀረ፡፡ በተጠበቀበት ጊዜ ቢቀርም ዘግይቶ በራሱ ጊዜ የሚወጣው "ሰብሮ ገብ" የሚሉት ፈንጣጣ አባቴን ያዘውና በጽኑ ታመመ፡፡ በተለይም በዓይኑ ላይ እጅግ ከብዶ ወጣ፡፡

የሕመሙ ክብደት በግራ በቀኝ የነበረውን ቤተ ዘመድ ትልቅ ጭንቀት ላይ ጣለ፡፡ ቀድሞ በጸብ ተለያይተው የነበሩት ሁለቱ ሴት አያቶቹ ይቅር ለእግዚአብሔር ተባብለው የልጅ ልጃቸውን በአንድነት ሆነው ማስታመም ጀመሩ፡፡ ከእናቱም፣ ከአባቱም ወገን የሚወለዱ አክስቶቹ ሁሉ ሰመገናኘትና ዕርቀ ሰላም ለማውረድ ቻሉ፡፡ ይህ መልካም አጋጣሚ ሆኖ ሳለ የሕመሙ ጥንካሬ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄዱና የዓይኑን ብርሃን ማድከሙ ግን ከባድ ሀዘን ሆነባቸው፡፡ የሚያምር ዞማ ፀጉርና የተዋቡ ትልልቅ ዓይኖች የነበሩት መልከ መልካሙ ቀይ ልጅ ለዓይነ ሥዉርነት አደጋ መቃረቡ ግልጽ እየሆነ መጣ፡፡ መላ ቤተሰቡ በተለይም ወላጆቹና አያቶቹ በሁኔታው በመጨነቃቸው በዚህ ጉዳይ ላይ አዘውትረው ይወያዩ ነበረ፡፡ ከዚህ የተነሳ ከዕለታት በአንዱ ቀን ወይዘሮ እማሁሽ ፤

"ዓይነ ሥውር ሆኖ እሾህ ሲወጋው፣ ዕንቅፋት ሲመታው፣ በዚህም ምክንያት ሲከፋው ሲያዝንና ሲተክዝ ከማየው አንድ ቀን ሞቶ ብቀብረው ይሻለኛል፡፡ አምላክ ቅዱስ ጊዮርጊስ ይህን ብታደርግልኝ መጋረጃህን እሰጣለሁ" ብለው ተሳሉ፡፡

የአባቱ እናት ወ/ሮ ተዋበች ደግሞ፣ "እማሁሽ እንዲህ አትበይ፣ በጎጃም እኮ ብዙ ስመ ጥር ዓይነ ሥዉር መምህራን ነበሩ፣ አሁንም አሉ፡፡ እሱ አይሙት እንጂ እንደነዚያ መምህራን ቤተ ክርስቲያንን እያገለገለ



ይኖራል፡፡ በተለይም አገሬ ዲማ ሰፊ ነው፣ ታላቅ ነው፣ አይሙት እንጂ የዓይኑ መጥፋት እጅግ አይጎዳውም፡፡ ስሙንም እያሉው ብዬዋለሁ፡፡ አምላክ ቅዱስ ጊዮርጊስ እንደ ቀደሙ ዓይነ ሥዉራን አባቶች ቤተ ክርስቲያንን እያገለገለ እንዲኖር ፈቃድህ ይሁን፡፡ እኔ ደግሞ ሕይወቱን አለምንሃለሁ፡፡ የለመንኩህን ብትፈጽምልኝ መጋረጃህን እሰጣለሁ፡" ብለው ተሳሉ፡፡

የእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ ወ/ሮ ተዋበች ዋሴ ምኞትና ልመና አደላ፡፡ እባቱ አያሌው ታምሩ ከሞት ተረፈ፣ ነገር ግን የዓይኑን ብርሃን አጣ፡፡ ይህ ሲሆን ዕድሜው ሦስት ዓመት ተኩል ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ኑሮው ከአባቱና ከአያቱ ከተዋበች ዋሴ ጋር እንዲሆን ተወሰነ፡፡ በዚህም ምክንያት ከቤተ ንጉሥ ወደ ኮኛ ተወሰደ፡፡ አቶ ታምሩ ከወይዘሮ እሞኘሽ ከተፋቱ በኋላ ትዳር አልያዙም፡፡

በኮኛ የሚገኘው የወይዘሮ ተዋበች ዋሴ ቤት ዙሪያውን በወንዶች ልጆቻቸው የተከበበ ነበር፡፡ ከአቶ ታምሩ በስተቀር ወንዶች ልጆቻቸው የየራሳቸውን ትዳር የያዙ ነበሩ፡፡ ሁለቱ ሴቶች ልጆቻቸው ደግሞ ባል አግብተው በሄዱባቸው አገሮች ይኖሩ ነበር፡፡ ከእያንዳንዱ ቤተሰብ የተወለዱት የልጅ ልጆቻቸው በርከት ያሉ ስለ ነበሩ ባዕድ ሳያስገቡ እርስ በርሳቸው ይጫወቱ ነበር፡፡

ለሁሉም ልጆች እማካይ መገናኛ የአያታቸው ቤት ሲሆን ዓይነ ስውሩ አባቴ ግን ከሌሎች የልጅ ልጆች በተለየ ሁኔታ የአያቱ ልዩ ክትትል ይደረግለት ነበር፡፡በዕድሜ የሚቀርቡት የአክስቶቹና የአጎቶቹ ልጆች አምስት ነበሩ፡፡ ዘውዴ እየለ፣ አስጠየቁ እንዳልፈር፣ ደጅይጥኑ ደሴ፣ ዓለሙ ካሣና ተመስገን ሙላቱ ይባላሉ፡፡ በተለይ ከደጅ ይጥኑ ደሴ ጋር ይግባባና ዐብሮ መጫወት ያዘወትር ነበር፡፡

እቴቴ ደጆ ይጥኑ ስለ ልጅነት ትዝታዋ እንደ ነገረችኝ ከሆነ ለጨዋታ ብለው ሰብስበው የከመሩትን አፈር አባቴ በእጆቹ እየዳበሰ የተለያየ ቅርጽ ያላቸውን ምስሎች መሥራት ይወድ ነበር፡፡ እዷ ደግሞ የተለያዩ ምስሎች እየሠራ የሚያጫውታትን አባቴን የመረበሽ ልማድ ነበራት፡፡

በዚህ ምክንያት የተከመረውን አፈር በትናበት "ጨዋታ ፈረስ" ብላ ትሸሻለች፡፡ አባቴም ከሸሸችበት እስክትመለስ ጠብቆ ይደበድባታል፡፡ በሁለቱ መካከል የሚፈጠረውን ጸብ የሚገላግሉት የአቴቴ ደጆይጥኑ አባት ደሲ የተመኘ በሚሰጡት ዳኝነት ዘወትር ለአባቴ የማድላት ነገር ይታይባቸው ነበር፡፡

የምድረ ግቢው ልጆች ተሰባሰበው ጨዋታ ሲሰፉ አባቴ የአክስቶቹንና የአጎቶቹን ልጆች ተሰብስቡ ይላቸውና በሰፈራቸው መሐል ከሚገኝ ዛፍ ዙሪያ ክብ እንዲሠሩ ያደርጋል፡፡ ዛፉ ላይ ተንጠላጥሎ ይወጣል፡፡ በዛፉ ቅርንጫፎች ላይ ተቀምጦ ወይም ቆሞ የተለያዩ ዘፈኖችና ተረቶችን ያሰማቸዋል፡፡ ሲጫወት ውሎ የምሳ ሰዓት ሲደርስ እያቱ ተዋበች ዋሴ ምሳ እንዲበላ ይጠሩታል፡፡ ምሳውን ተቀብሏቸው ወደ ደጅ ይጥኑ ይመለሳል፡፡ ከዚያም አብረው ይበላሉ፡፡ ይሄ የዘወትር ልምዳቸው ሲሆን ብቻውን መመገብም በፍጹም አይወድም ነበር፡፡ በዚህ ጠባዩ ምክንያት እያቱ ለእርሱ ምግብ ለማቅረብ ሲያስቡ ከሌሎች የልጅ ልጆቻቸው መሐል አንዱን መጥራት ነበረባቸው፡፡ አለዚያም እሱን ራሱን "ሄደህ የሚያበላህ ጠርተህ ና" ይሉት ነበር፡፡

ቀን ቀንን እየወለደ አባቴም እያደገ ሲሄድ እያቱና አባቱ ስለ እርሱ መጻኢ ዕድል መጨነቅና መወያየት ጀመሩ፡፡ በነባሩ ልማድ መሠረት ግደኑ ሥጪራንን ወደ ትምህርት ቤት መላክ ከሁሉ የተሻለ ምርጫ ቢሆንም እርሱ ግን ከአባቱ ለመራቅ አለመፈለጉን አዘውትሮ ይናገር ስለነበረ ጨክነው በቶሎ ወደ ትምህርት ቤት ለመላክ ከብዷቸውነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በጊዜው የነበሩት ትምሕርት ቤቶች ከኰኛ የነበራቸው ርቀት ሕፃኑ ከቤተሰብ ጋር ሆኖ ሊማር የሚችልበትን ዕድል የሚሰጥ ስላልነበረ ሌላው የጭንቀታቸው ምክንያት ነበረ፡፡

የኰኛና የአካባቢው ሰዎች ልጆችን ወደ ትምህርት ቤት ለመላክ ሲፈልጉ ከዲማና ከደብረ ወርቅ የቀረበ ቦታ አልነበረም፡፡ የተዋሕዶ እምነትን የሚከተል ዲማን፣ ቅባትን የሚከተል ደግሞ ደብረ ወርቅን መምረጡ የተለመደ ስለ ነበረ፣ አባቴ ሊላክ የሚችለው ወደ ዲማ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነበረ፡፡ እሱን ትምሕርት ቤት በመላክና ባለመላክ፣



በመንገዱ ርቀትና ተያያዥነት በነበራቸው ጉዳዮች ላይ ቤተሰቡ ሲወያይ የሚሰማው ሕፃን ይህ ጉዳይ በተነሣ ቁጥር እያለቀሰ ያስቸግር ነበር፡፡ በተለይ አባቱ በዚህ ጉዳይ ላይ የነበራቸውን አቋም ለመለየት ተቸግረው ቆዩ፡፡ እንዲያውም አንዳንዴ የትምህርት ቤት ጉዳይ ሲነሣ አባትና ልጁ ተያይዘው ይላቀሱ ነበር፡፡

# ምዕራፍ ፪

# የትምህርት ቤት ሕይወት

## ፲፱፻፳፬ - ፲፱፻፵፰



## ዲማ"ለጆሮ ከባድ ለዓይን ቀላል"

ዕድሜ ለ "ፍቅር እስከ መቃብር" ፤ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ዲማን የማያወቅ ሰው ይኖራል ማለት ዘበት ነው፡፡ በክቡር ዶክተር ሀዲስ ዓለማየሁ ብዕር ተጽፎ በወጋየሁ ንጋቱ አንደበት የተተረከው ይህ መጽሐፍ ለንደ ሰብለወንጌልና በዛብህ ፍቅር ሁሉ፤ ዲማንም አይረሴ አድርጐታል፡፡

"ወይ ዲማ ለጆሮ ከባድ ለዓይን ቀላል ማለት አንተ ነህ!" ብሎ የፍቅር እስከ መቃብሩ በዛብህ የተገረመበትን ዲማን ለጆሮ ከባድ ያደረገውየታላላቅ ሊቃውንት መፍለቂያ የሆነው ጥንታዊው የቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም ወይም ደብረ ድማኅ ነው፡፡ ደብረ ድማኅ በምሥራቅ ጐጃም በብቸና አውራጃ ውስጥ ይገኛል፡፡ ዲማን የቀረቆሩት መንፈሳዊ አባት አቡነ ተክሥተ ብርሃን ይባላሉ፡፡ አቡነ ተክሥተ ብርሃን የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የመንፈስ የልጅ ልጅ ሲሆኑ የቀደመ ስማቸው በኪሮስ ይባል ነበረ፡፡ ተክሥተ ብርሃን ከጊዜ በኋላ የወጣላቸው ስም ነው፡፡

ይህ ስም የተሰጣቸው በምክንያት ነው፡፡ በምድረ ጎጃም እየተዘዋወሩ ሲያስተምሩ ባለ አንድ ቀን "ነድ አጥራ" በሚባል ቦታ የማስተማር ሥራቸውን ሲያከናውኑና ምእመናንን አሳምነው ሲያጠምቁ ዋሉ፡፡ ከሰው ብዛት የተነሣ የማጥመቅና የማቁረብ አገልግሎታቸውን ሳይጨርሱ ጀምበር ገባች፡፡ በዚህን ጊዜ ከሰማይ ብርሃን ወርዶ እንዳበራላቸውና በዚህም ምክንያት ተክሥተ ብርሃን እንደተባሉ ታሪካቸው ያስረዳል፡፡

አቡነ ተክሥተ ብርሃን ከሸዋ ወደ ጐጃም ሲንቀሳቀሱ ይዘዋት የነበረችውን የእመቤታችንን ታቦት ወደ ጐጃም ሲገቡም ይዘዋት በመዝለቃቸው ዲማ ሲደርሱ ታቦቲቷን በዋሻ ውስጥ አስቀምጠው ሲያገለግሉና ሲያስተምሩ ለ ፲፭ ዓመታት ቆይተዋል፡፡ እሳቸው ባረፉ ጊዜ አቡነ ቀማስ ተኳቸው፡፡ እሳቸውም ታቦተ ጊዮርጊስን ከሸዋ አምጥተው አሁን ባለበት ቦታ ላይ እንዲተከል አደረጉ፡፡ ታቦተ ማርያምንም በዚሁ ቤተ መቅደስ አስቀመጡ፡፡ ይህ የተደረገበት ዘመን የአፄ ይሥሐቅ ዘመነ መንግሥት ነበረ፡፡

ከአቡነ ቶማስ ጀምሮ እስከ አቡነ ተክለ አልፋ ድረስ መነኮሳቱ በአንድነት ገዳም ሥርዓት የኖሩ ሲሆን በቀሪው ርስት ላይ ሕዝቡ ይኖርበት ነበረ። በአፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ወደ ገዳምነት ያደገው ይህ ቤተ ክርስቲያን በአፄ ይስሐቅ ዘመን ደብር ወገዳም ተብሎ ብዙ ቅፈፍ ተሰጥቶት በተስፋፋ ሁኔታ የደብርና የገዳም ሥርዓት የሚከናወንበት ሆኗል።

በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት መንበርነቱ የሚታወቀው ደብረ ድማኅ ከፍተኛ የዕውቀት ማእከል እንደ መሆኑ መጠን ብዛት ያላቸው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሊቃውንት መፍለቂያ በመሆን አገልግሏል። ይህ ቦታ የጸዋትወ ዜማ፣ የግዕዝ ቋንቋና ቅኔ፣ ትምህርተ ሃይማኖት፣ የብሉያት፣ የሐዲሳት፣ መጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኮሳት ትርጓሜ ትምህርት በስፋትና በጥልቀት ሲሰጥበት የኖረ መሆኑንና እዚያ ተምረው እድላቸው እንደፈቀደ በቤተክህነት ወይም በመንግሥት ሥራ የተሰማሩ ብዙዎች መሆናቸውን የሚገልጡ ጽሑፎች አሉ።

ደብረ ድማሕ እየተባለ በሰማዕቱ በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም የተደበረ ቢሆንም በዚያው ቦታ ላይ ኖረው ታላላቅ መንፈሳዊ ተጋድሎ በማድረግ ከፍተኛ የጽድቅ ሥራ የሠሩት ጻድቁ አቡነ ተክለ አልፋም ገዳም ተገድሞላቸዋል። ጻድቁ አባ ተክለ አልፋ እንደ ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ያሉ ኢትዮጵያዊ ጻድቅ ናቸው።

የደብረ ድማኅ ፳ኛው መምህር የነበሩት አቡነ ተክለ አልፋ ገዳሙን ለ፴፭ ዓመታት ያስተዳደሩ ሲሆን ባደረጉት መንፈሳዊ ተጋድሎ ብዙት ያላቸው ገቢረ ተአምራት የተፈጸመላቸው በመሆኑ የጻድቅነት ማዕረግ ተሰጥቷቸው ገዳምነቱ የእሳቸው መታሰቢያ ለመሆን ችሏል። ጻድቁ አቡነ ተክለ አልፋ ያረፉት ታህሣሥ ፳ ቀን በመሆኑ የዕረፍታቸው መታሰቢያ በየዓመቱ በዚሁ ዕለት በዲማና በአካባቢው በከፍተኛ ድምቀት ይከበራል።

በጉጃም ውስጥና ከጉጃም ውጪ የሚኖሩ ብዙት ያላቸው ኢትዮጵያውያን የበታው ተወላጆች በዓሉን ለማክበር ወደዚያ ይሄዳሉ።



አጋጣሚውን በመጠቀምም በዲማ ከሚኖሩ ዘመዶቻቸው ጋር ይጠያየቃሉ። ከዐቅም በላይ የሆነ ችግር የገጠመው ሰው ካልሆነ በቀር ከዓመታዊው የአቡነ ተክለ አልፋ ክብረ በዓል የሚቀር የዲማ ተወላጅ አይገኝም። ይህን በዓል ለመሳተፍ የሚጓዘው ሕዝባዊው ምእመን ብቻ ሳይሆን የጻድቁን ረድኤትና የገዳሙን ክብርና ደረጃ የሚያውቁ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና መዘምራንም ከአዋሳኝ አገሮች ሁሉ ሳይቀር መንፈሳዊ አገልግሎት ለመስጠት ወደ ዲማ ይጎርፋሉ።

የዲማ አስተዳደር ሁሉን አሳታፊና ከፍተኛ ሥርዓት የነበረው መሆኑን አባቴ ነግሮኛል። ቀደም ብሎ የነበረው ቤተ ክርስቲያን እስከ ግራኝ አህመድ ወረራ ዘመን የንፍሮ ገዳም የነበረ ሲሆን ከግራኝ አህመድ ወረራ በኋላ ግን በአካባቢው የሚኖሩ ባለርስቶችን በማሳተፍ ደብር እንዲሆን ተደርጓል። በግራኝ አህመድ ዘመን የገዳሙ መምህር የነበሩት አባ ተክለ አልፋ በጦርነቱ ምክንያት አጼ ልብነ ድንግልን ተከትለው እስከ ደንቢያ ድረስ ተጉዘዋል። ጦርነቱ አልቆ ወደ ዲማ ሲመለሱ መነኮሳቱ ሸሽተው ታቦቱን ባለርስት ሲጠብቀው ስማግኘታቸው ጠቅላላ የመነኮሳት ብቻ የነበረውን አገር አካፍለው አመጣጥነው ግማሹን ለባለአርስት ግማሹን ደግሞ ለመነኮሳት ሰጡ።

የአካባቢው የበላይ ጠባቂ የእጎዛ መምህር የሚባለው መነኩሴ ሆኖ ከበታቹ ግን በአንድ ፊት መነኮሳት በሌላ በኩል መዘምራን የሚሠየሙበትና የሚያገለግሉበት ሥርዓት አለ። በመነኮሳቱ በኩል ያለውን መነኮሳቱና መምህሩ ብቻ መክረው ይሾማሉ። በውጪው መዘምራኑን በሚመለከተው ግን መነኮሳቱንም ሕዝቡንም ባሳተፈ ሥርዓት ምርጫ ይከናወናል። የሚመረጡት ሰዎች የማዕረግ ስም አላቸው። የማዕረግ ስሞቹ ግበዝ[6] መጋቢና[7] ራቅማሠራዩ[8] ይባላሉ።

---

[6] መጋቢ፦ ይህ ስያሜ የሚሰጠው ሰው ከመምህሩ በታች በመሆን [illegible] (መቀነን) የሚበላውንና የሚጠጣውን ሰው [illegible]

[7] ራቅማሠራዩ፦ ይህ ስያሜ የሚሰጠው ሰው እሌ መምህር ነው። ራቅማሠራዩ የውስጥና የውጪ ተብሎ ስሁለት የሚከፈልበት ጊዜም ነበረ። የውስጡ በመምህሩና በመነኮሳቱ የውጪው ደግሞ በመምህሩና በመዘምራኑ መካከል ያለው ግንኙነት የተቀላጠፈ እንዲሆን ይረዳ ነበር።

ከነዚህ በተጨማሪ ሊቀ አበው[9] በመባል የሚታወቅ ማዕረግም ነበረ፣ የሚያገለግሉት ሦስት ሦስት ዓመት ሲሆን ለእያንዳንዳቸው የተመደበ የተግባር ዝርዝርም ነበራቸው፡፡

እያንዳንዱ የሦስት ዓመት የአገልግሎት ዘመን ዙር ሲያበቃ ሕዝቡና ካህናቱ ተሰብስበው ባሉበት ከመዘምራት መካከል ሌሎች አዳዲስ ሰዎች ራሳቸውን ለምርጫ ዕጩ አድርገው ያቀርባሉ፡፡ ያለፈ ታሪካቸውንና የወደፊት ዕቅዳቸውን ዘርዝረው በመናገር የምርጫ ዕድል እንዲሰጣቸው ይጠይቃሉ፡፡

ከዚህ በኋላ ራሳቸውን በዕጩነት ያቀረቡት ሰዎች ከሕዝቡ መካከል ወጥተው እንዲገለሉ ይደረጋል፡፡ በመቀጠልም የተሰበሰበው ሕዝብ ስለሰዎቹ ይመክራል፡፡ ክርክሩና ምክክሩ ካበቃ በኋላ ከዚያው ከሕዝቡ መካከል ዘጠኝ ሰዎች ለአስመራጭነት ይሠየማሉ፡፡ እነዚህ ዘጠኝ ሰዎች ምርጫውን በሀቀኝነት ለማስፈጸም በህዝቡ ፊት ቃል ገብተው በእግዚአብሔር ስም ምለው ለአገር ይጠቅማሉ ብለው ያመኑባቸውን ሦስት ሰዎች ይመርጣሉ፡፡ ምናልባት ቀደም ብሎ በአገልግሎት ላይ ከነበሩት ሹማምንት መካከል በቀጣይነት ቢያገለግል ይበጃል የሚባል ሰው ካለ በድጋሚ የመመረጥ ዕድል ይሰጠዋል፡፡ አለበለዚያ ግን በሙሉ ከአዳዲሶቹ ዕጩዎች ይመረጣሉ፡፡

ምርጫው ከተጠናቀቀ በኋላ ሕዝቡ በሙሉ ድምጽ እጨብጭቦ ተቀብሎ፣ የማዕረግ ልብስ አልብሶ በየቤታቸው ያስገባቸዋል፡፡ ሥልጣናቸውን ክብራቸውን መብታቸውን ያውቅላቸዋል፡፡ ትዕዛዛቸውንም በሙሉ ይቀበላል እንጂ አንድም የሚቃወም የለም፡፡ በሦስት ዓመቱ የሥልጣን ዘመናቸውም በሙሉ ልቡ ይታዘዛቸዋል፡፡

---

[8] [illegible]

[9] [illegible]



## ዲማና በዓለ ተክለ አልፋ

በዓለ ተክለ አልፋ ለዲሞች የተለየ ነው፡፡ የገና ጾም ላይ ቢውልም ክብረ በዓሉ ደማቅ ነው፡፡ ለዚህ መንስዔው ለረጅም ጊዜ የተነፋፈቁ ዘመዳሞችም የሚገናኙት በዚሁ ዕለት በመሆኑ ጭምር ነው፡፡

ወይዘሮ ተዋበች ለጉዞ ብቁ የሆነውን የቤተሰብ አባል በሙሉ እያስከተሉ በየዓመቱ ወደ ዲማ የመጓዝ ልምድ ነበራቸው፡፡ በዚሁ መሠረት አባቱ የዘጠኝ ዓመት ልጅ ሳለ አብሯቸው እንዲሄድ ፈቀዱለትና ዲማ ሄዱ፡፡

በተክለ አልፋ ዋዜማ ከኩኛ ወደ ዲማ የተጓዘው ቤተሰብ የወይዘሮ ተዋበች ታናሽ እህት ከሆኑት ከወይዘሮ ደብሪቱ ዋሴ ቤት ጠቅልሎ ገባ፡፡ ወይዘሮ ደብሪቱም ለበዓሉ ያዘጋጁትን ጠላ፣ አረቄ ዳቦና ቆሎ አቅርበው መስተንግዷቸውን ጀመሩ፡፡ ቀድሞ የቀረበው ቆሎና ዳቦ ሳይጋመስ ደግሞ ከጤፍ ዱቄት የተሰራው እንጀራ በየመሶቡ ላይ እየተከመረ ቀረበ፡፡ የምጣድ ሽሮ፣ ማርሳ፣[10] ውጥሜ፣[11] አልበት፣[12] የሽምብራ አሳ፣ የሱፍና የተልባ ፍትፍት ለንግ ቃሪያውም ሁሉ ሳይቀር ቀረበ፡፡ መስተንግዶው በሳቅና ጨዋታ እየተዋዛ ከተጠናቀቀ በኋላ ከተሰበሰው ሰው መሀል በዕድሜ ከፍ የሚሉ ሦስት ሰዎች ምርቃት አቀረቡና ገበታው ከፍ አለ፡፡ የምግብ ሥነ ሥርዓቱን መጠናቀቅ ሲጠብቁ የነበሩት አቶ ታምሩ ከተቀመጡበት ተነሱና፣

"በሉ እንግዲህ እናንተ ተጫወቱ እኔ ወደ ቤተክርስቲያን ልሂድ" እያሉ ተነሱ፡፡ "አመሻሽተህ ትመለስ ነው ወይ ልታድር ነው?" የወይዘሮ ተዋበች ጥያቄ ነበረ፡፡"የለም! ኸዚያው ልደር እንጂ" አሉ አቶ ታምሩ፡፡

---

[10] ከአተር ክክ የሚሰራ አልጫ ወጥ በጐጃም "ማርሳ" ይባላል፡፡ "ር" ሲነበብ አይጠብቅም፡፡

[11] ውጥሜ ፤ ከሽንብራ ዱቄት የሚሰራ ሲሆን ተዘጋጅቶ ሲቀርብ ከዕንቁላል የተሠራ ፍርፍር ይመስላል፡፡

[12] አልበት ከባቄላ ዱቄት! ከሱፍ ውሃና ከሰናፍጭ የሚሠራ የጾም ምግብ ነው፡፡

አቶ ታምሩ ሥር ሽጉጥ ብሎ ተቀመጠ የነበረው የዚያን ጊዜው ታዳጊ ህፃን አባቴ ከተቀመጠበት እመር ብሎ ተነሳና፣ "እኔም ፤ እኔም አብሬህ እሄዳለሁ እያዬ! አሳቸው፡፡ ጥያቄውን የተቃወመ አልነበረም፡፡

አቶ ታምሩ ምንም እንኳ የቤተ ክህነት ሰው ባይሆኑም ፈሪኀ እግዚአብሔርን የሚያስቀድሙ፣ ሃይማኖተኛና በተሰበረ መንፈስ የሚኖሩ ትሑት ሰው ስለነበሩ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት በቅርበት መከታተል ያዘወትሩ ነበር፡፡ በመሆኑም ልጃቸውን አስከትለው የበዓለ ተክለ ዓልፋን ዋዜማ ለማክበር ወደ ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አመሩ፡፡

አባት የልጃቸውን እጅ ይዘው እየመሩ፤ እሱም የተለያዩ የልጅነት ወሬዎች እያወራቸው፣ እልፎ አልፎም ከእጃቸው እያመለጠ ፈጠን ፈጠን እያለ እየቀደማቸው፣ ደግሞ ቆም በማለት እየጠበቃቸው መንገዳቸውን ወደ ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ቀጠሉ፡፡

በመንገዳቸው ላይ ካገኟቸው ከቀዬው ኑዋሪዎች አብዛኛዎቹ ከአቶ ታምሩ ጋር የሚጓዘው ዓይነ ሥዉር ታዳጊ ልጃቸው መሆኑን አላጡትም ነበር፡፡ ዐምስትና ስድስት ዓመታት ወደ ኋላ በዚያ አካባቢ የደረሰው የፈንጣጣ ወረርሽኝና በየሰዉ ቤት ጥሎ ያለፈው አሳዛኝ ትዝታ ከብደቱ ይለያይ እንደሆነ ነው እንጂ የሚረሳ አልነበረም፡፡ ፈንጣጣ ይዞት በቀላሉ ከዳነው ሰው ጀምሮ፣ በቆዳው ላይ ጠባሳ ጥሎበት የለፈ፣ እንደ አባቴ የዓይኑን ብርሃን የተቀማና ከነአካቴው ህይወቱንም ያጣ ብዙ ሰው ነበረ፡፡

አባትና ልጅ የበዓለ ተክለ አልፋን ዋዜማ ለመታደም ወደ ቤተ ክርስቲያን የጀመሩትን ጉዞ ጨርሰው ከቦታው ሲደርሱ ቀኑ እየመሸ ነበር፡፡ የዋዜማውን የምሥጋና ዝማሬና ጸሎት ሲከታተሉ አደሩ፡፡ ቅዳሴውንና የታቦቱን ሥርዓተ ንግሥ በአግባቡ ከተካፈሉ በኋላ እናታቸውና ዘመዶቻቸው ወደ ተሰባሰቡበት ወደ አክስታቸው ወደ ወይዘሮ ደብሪቱ ቤት ተመለሱ፡፡ በዚያም ከድግሱ ተቋድሰው፣ ከጨዋታው ተካፍለው በተጨማሪም ደግሞ በዲማ የሚኖሩ ሌሎች



ዘመዶቻቸውን ከጎበኙ በኋላ የመጨረሻ ጉብኝታቸው በነበረው በወይዘሮ ጉዳዬ ጎበዜ ቤት ወደ አገራቸው ለመሄድ ዝግጅት ጀመሩ፡፡

ዘመድ ከዘመዱ መሰነባበት ሲጀምር አባቴ ወደ ኰኛ ከሚመለሱት ጋር አልሄድም ብሎ እምቢ አለ፡፡ ለምን እምቢ እንዳለ ሲጠየቅ ትምሕርት ቤት እገባለሁ የሚል ምክንያት ሰጠ፡፡ አባቴን "ትምሕርት ቤት ግባ" ወይም" ወደ ኮኛ አትመለስ፣እዚህ ቅር" ብሎ የመከረው አንድም ሰው አልነበረም፡፡ምን ተሰምቶት ትምሕርት ቤት እገባለሁ እንዳለ የሚያውቅ ሰውም አልነበረም፡፡ እሱም ቢሆን ሕፃን ስለነበረ በጊዜው በሰተሰማው ስሜት ብዙ አያስታውስም፡፡ ነገር ግን በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በተካሄደው የተክለ አልፋ በዓል ላይ የመገኘቱ ሁኔታ የፈጠረበት አንዳች በጎስሜትና የልጅነት ጉጉት ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል፡፡

የአባቴን ትምሕርት ቤት መግባት እጥብቀው ይፈልጉና ይመኙ ከነበሩ ሰዎች መካከል ዋነኛዋ እያቱ ወይዘሮ ተዋበች የነበሩ ቢሆንም ውሳኔውን ለመቀበል ግን ደስተኛና ፈቃደኛ ሆነው አልተገኙም፡፡ በራሱ ጊዜ ድንገት ወስኖ ወደ ኮኛ አልመለስም ሲላቸው በዚያ የሕፃንነት ዕድሜው ጥለውት መሄድ አላስችል አላቸው፡፡ ይልቁንም ደግሞ ከአባቱ ላለመለየት የነበረበትን ሰቀቀን ሲያስቡት ትተውት ቢሄዱ እንኳ ከአንድ ወይም ከሁለት ቀን በኋላ አባቱን ናፍቆ ማስቸገሩ የማይቀር መሆኑን አመኑ፡፡ስለዚህም በፍጹም ትቼው አልሄድም ብለው አሻፈረኝ አሉ፡፡ አባቱ አቶ ታምሩም የእናታቸውን ሐሳብ ደገፉ፡፡

ዘመዶቻቸው ግን "እንዴት እርሱ ልማር እያለ እናንተ ይዛችሁት ትሄዳላችሁ?" በማለት ክርክር ገጠሙ፡፡ ሆኖም ግን ሕፃኑን ትተው ለመሄድ በጄ አላሉም፡፡ በዚህ መሐል የቤቱ ባለቤት ወይዘሮ ጉዳዬ "እመይቴ እስቲ ለእኔ ይተዉትና ስምንት ቀን እንየው። ከዚያም በኋላ ለገበያ ሲመጡ ሁኔታውን አይተው ይወስናሉ፤" ብለው አስቀሩት፡፡

አንድ ሰንበት፣ ሁለት ሰንበት፣ ሦስት ሰንበት፣ ወር እየተባለ ጊዜው ነጐደ፡፡ ነገር ግን የተፈራው ሁሉ ቀርቶ የዲማ ቆይታውን እየለመደው

ሄደ፡፡ አባቱን መናፈቅና ሲጠይቁት በሚመጡባቸው ቀናት የመባባት ሁናቴ ቢያሳይም ትምህርቱን ትቶ ለመሄድ ግን አልፈለገም፡፡

የትምህርት ቤቱን ሕይወት እስኪለማመድ አባቱና አያቱ እንጀራ በአገልግል እየያዙ ይጠይቁት ነበር፡፡ ይልቁንም ወይዘሮ ጉዳዬ ከልጆቻቸው ሳይለዩ በጥሩ ሁኔታ ስለ ያዙት ለአንድ ዓመት ያህል ያለምንም ሐሳብ ትምህርቱን ለመከታተልና አካባቢውን ለመልመድ ቻለ። ከቤተሰቡ ርቆ፣ መናፍቅ ረስቶ ወደ ትምህርቱ ብቻ እንዲያተኩር የረዱትን የወይዘሮ ጉዳዬን ውለታ እያስታወሰ ስለ እርሳቸው በተነካ ቁጥር ያመሰግናቸው ነበር፡፡

በመጀመሪያው ዓመት የዲማ ቆይታ ማብቂያ ላይ ኑሮውን በዐጸደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቻ እንዲወሰንና ከዘመድም ሆነ ከወገን ተስፋ እንዳይጠብቅ የሚያስገድዱ ችግሮች ገጠሙት፡፡ ከዚህ የተነሳም ወደ ወይዘሮ ጉዳዬ ቤት መሄዱን አቆመ፡፡ ከገጠሙት ችግሮች ዋነኛው የአባቱ በጠና መታመም ሲሆን፤ አያቱም ልጃቸውን በማስታመም ሥራ፤ በእርጅናና በዐቅም ማነስ የተነሣ እንደ ወትሮው ቶሎ ቶሎ ሊጠይቁት አልቻሉም፡፡ በተለይ የአባቱ መቅረት ከዘመድ የሚጠብቀውን ተስፋና ቅርርብ እንዲገታና ተስፋውን በትምሕርት ቤት አካባቢ በነበረው ሕይወት ላይ ብቻ እንዲያተኩር አደረገው፡፡



## የየንታ ማርቆስ ህልም

አባቱ ትምህርት በጀመረባቸው የመጀመሪያ የትምህርት ዓመታት ከመምህራኑ እግር ሥር ተቀምጦ የየቀን ትምህርቱን ከመከታተል ይልቅ በአብዛኛው ወደ ጨዋታ የማድላት ጠባይ ነበረው፡፡ በመሆኑም ብዙ ጊዜ ከትምህርት ገበታው ላይ አይገኝም ነበር፡፡ ሲጫወት ውሎ ማታ ለመኝታ ከጓደኞቹ ጋር ሲገናኝ ዐብሮ እደጉና ጓደኛውን መሪጌታ እውነቱን[13] እየጠየቀ ያጠናል፡፡ ትምህርት የመቀበል ችሎታው ፈጣን ስለነበረ ከመምህራኑ የሚፈለግበትን ውጤት አሟልቶ ይገኝ ነበረ፡፡

አባቴ ትምህርት ትቶ ወደ ጨዋታ እንዳይሄድ የሚመክሩትን ሰዎች "ማታ ከእውነቱ እማገኘውን!" እያለ ይመልስላቸው እንደ ነበረ ዛሬ በሕይወት ያሉ፣ ሲወራም የሰሙ የአካባቢው ሰዎች ያስታውሳሉ፡፡ አለቃ ፈለቀ ተገኝ የተባሉ ለአባቴ ዝምድና የነበራቸው ሰውም እየተቆጣጠሩት ለጨዋታ ከሄደበት ፈልገው በማምጣት ትምህርቱን በሥርዓት እንዲከታተል አድርገዋል፡፡

አባቴ ያለምንም ጠባቂና ታዛቢ በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ ሁሉ እያለፈ አካባቢውን ያጠናና ይለማመድ ነበር፡፡ ከትምህርት ሰዓት ውጪ በሚያገኘው ነጻ ሰዓት በቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያና በአካባቢው ያሉ ነገሮችን የመመርመር ጠባይ ነበረው፡፡ ከጓደኞቹ ተለይቶ ወደ ገደል አፋፍ፤ ወደ ወንዝ ውሃ ይሄዳል፡፡ ገደሉ ጋ ሲደርስ፤ በደረቱ ተኝቶ ፊቱን ወደ መስኩ፤ እግሮቹን ወደ ገደሉ አድርጎ ወደ ኋላው በመሳብ እግሩን ማሳረፊያ ቦታ ይፈልጋል፡፡ እግሩን የሚያሳርፍበት ቦታ ሲያጣ ወደ መስኩ ተመልሶ ይወጣል፡፡ ወደ ወንዝ ሲሄድም ልብሱን አወላልቆ ወደ ውሃው ይገባል፤ ልክ እንደገደሉ እግሩን ማሳረፊያ ለማግኘት ይሞክራል፤ ሲያጣ ተመልሶ ይወጣል፡፡

[13] መሪጌታ እውነቱ ዓይነ ሥዉር ነበሩ፡፡ ዲማን ጊዮርጊስን በቅኔ መምህርነት አገልግለዋል፡፡

ትልቅ ሰው ከሆን በኋላ ያንን ያለፈ ሁኔታ እያስታወሰ ያስ እናትና አባት ወይም ሌላ የቅርብ ተንከባካቢ ጥቢቃ በሕፃንነት አእምሮው ካከናወናቸው ከእነዚያ አደገኛ ሙከራዎች ጠብቆ ያሳደገውን የእግዚአብሔርን ውለታ አዘውትሮ ያደንቅ እንደነበረ እኔም ለመገንዘብ ችያለሁ፡፡

መምህራኑ ትምህርትን ፈጥኖ በመቀበል ችሎታው፣ በመልካም ጠባዩና በዕድሜው ታናሽነት ይወዱትና ይጠነቀቁለት ነበር፡፡ አብዛኛዎቹ በገዳሙ ውስጥ ይገኙ የነበሩ ሊቃውንትና መምህራን ዓለምን የሚመረምሩበትና የሚረዱበት ከፍተኛ መንፈሳዊ ሰብእና ነበራቸው፡፡ እነርሱ ከእያት ቅድመ አያት የተረከቧትን ታላቂቱን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሙሉ የእምነት፣ የማንነትና የምንነት ቅርሷ ጋር የሚረከቧቸውን ተተኪ ልጆች በተሟላ ሰብእና ቀርጸው የማሳደግና በእግራቸው የመተኪት ግዴታቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ ስለነበሩ የሚያስተምሯቸውን ልጆች በእግራቸው ለመተካት በርትተው ይሠሩ ነበር፡፡ በመሆኑም ከሚሰማቸው ጥንቃቄ፣ መንፈሳዊ ግዳጅና ኃላፊነት የተነሣ ብሩህ እእምሮና መልካም ጠባይ ባላቸው ተማሪዎቻቸው ላይ የማተኮርና እልፎ ተርፎም በጸሎት የእግዚአብሔርን ፍቃድ የመጠየቅ ልምድ ነበራቸው፡፡ በዚህ መሠረት ብዙ ታላላቅ መንፈሳውያን አባቶችና ሊቃውንት መምህራን አባቴን በልዩ ጥንቃቄ እየጠበቁ በማስተማር፣ በመምከር በመጸለይ አሳድገውታል፡፡

በተለይም የኔታ መምህር ማርቆስ ብርሃኑና የኔታ መምህር እልማው የተባሉት ታላላቅ መንፈሳውያን አባቶች ስለ እርሱ አጥብቀው ይጸልዩ ነበር፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከደረሱ መናንያን ባሕታውያን መካከልም በልዩ ትኩረት የሚከታተሉትና የሚጸልዩለት ብዙዎች ነበሩ፡፡ ለወልደ ያዕቆብ ዮሴፍ የግብጽ ረኀብ፣ለዳንኤል ነቢይ የሁለቱ የንጉሥ አገልጋዮች መፃኢ ዕድል እንደተገለጠላቸው ሁሉ፤ ስለ አባቴ ይጸልዩ ከነበሩ መንፈሳውያን አባቶች መሐልም መፃኢ ዕድሉን የሚመለከቱ መንፈሳዊ ምስጢሮች የተገለጡላቸው አባቶች እንደ ነበሩ በርካታ ሰዎች የሚያውቁትና የሰሙትን ምስክርነት በተለያየ ወቅት



ገልጠዋል፡፡ ከነዚህ መንፈሳዊ ምስጢሮች መካከል የእባቴ ቅኔ አስተማሪ የነበሩት አለቃ ማርቆስ ብርሃኑ ያዩት ህልም አንዱ ነው፡፡

የኔታ አለቃ ማርቆስ ከእርሳቸውና ከመምህር ወልደ ኪዳን ዘንድ ቅኔ ሲቆጥር የነበረውን አባቴን በጣም ይወዱት ነበር፡፡ ከብዙዎቹ የቅኔ ተማሪዎቻቸው በዕድሜ ትንሹ ከመሆኑ ጋር የአእምሮው ብሩህነትና በዚያ ዕድሜው ይታይበት የነበረው መንፈሳዊ ሰብዕና እንኳ እንደሳቸው ላለ ታላቅ አባት ለሌሎችም የሚሰወር ስላልነበረ አብዝተው ይጠነቀቁለት ነበር፡፡

አንድ ቀን የኔታ ማርቆስ ሕልም አለሙ፡፡ ተማሪያቸው እያሌው በጅብ ሲበላ ነበር በሕልማቸው ያዩት፡፡ ጅብ የተማሪያቸውን አእምሮ ከጭንቅላቱ እያወጣ ሲበላው በማየታቸው ደንግጠው ከዕንቅልፋቸው ነቁ፡፡ ሕልሙን እያሰቡ ያ የሚወዱት ተማሪ ምን ሊያገኘው ይሆን? እያሉ ሲጨነቁ ካደሩ በኋላ በጠዋት ተቻኩለው ከቤታቸው ወጡ፡፡ ባሕታዊውን የኔታ እውነቴን ለማማከር ነበር አካሄዳቸው፡፡

በዲማ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ቅኔ ቤትና በመጽሐፍ ትምህርት ጉባኤዎች መካከል ሦስት ወይራዎች ነበሩ፡፡ እነዚህን ወይራዎች ባሕታዊው የኔታ እውነቴ ከልለው በዓት አድርገዋቸው ስለ ተማሪዎች እየጸለዩ ይኖሩ ነበር፡፡ አለቃ ማርቆስም ሕልማቸውን እያሰላሰሉ እንዲህ ያለውንስ ሕልም ለደገኛ[14] ሰው ማማከር ይገባል በማለት ወደ እሳቸው ሄዱ፡፡ የኔታ እውነቴ የየኔታ ማርቆስን መረበሽና መጨነቅ ገና ሲያዩአቸው የተገነዘቡት ባሕታዊ፤ "ማርቆስ! ምነው ተጨንቀሃል ደንግጠሃልሳ?" ሲሉ ጠየቁቸው፡፡ የኔታ ማርቆስም ያዩትን ሕልምና ጭንቀታቸውን አጫወቷቸው፡፡

"አይዞህ አትደንግጥ ሕፃኑ ምንም ክፉ ነገር አያገኘውም ይልቁንም ትልቅ ሰው የሚሆን ነው፣ ጅብ የሕዝብ ምሳሌ ነው፡፡ ይህ ልጅ ትልቅ ደረጃ ደርሶ ሕዝብን በአእምሮው የሚጠቅም ይሆናል፡፡ በእሱ አእምሮ

14 [illegible]

ብዙ ሕዝብ ይጠቀምበታል፡፡ ጠብቀው ከጊዜው ጊዜ ደርሰህ ታላቅ ነገር በእርሱ ሲገለጥ ታያለህ፡፡" ብለው ተረጕሙላቸው፡፡ "ያየኸውም ይሁንለት ይደረግለት" ብለው ህጻኑን ተማሪ መረቁት፡፡ አለቃ ማርቆስም በየንታ እውነቱ ትርጕም ተደስተው ተመለሱ፡፡

አለቃ ማርቆስም ለብዙ ጊዜ ይህን ሕልምና ፍቺ በምስጢር ይዘውት ኖሩ፡፡ የኋላ ኋላ ያ ሕፃን የቅኔ ተማሪያቸው አድጎ ትልቅ ሰው ሆኖ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ከሆነችው ከአዲስ አበባ ድረስ ሄዶ ስለ ሃይማኖት ተጠያቂና ተደማጭ መምህር መሆኑን ለማየት እግዚአብሔር አድሏቸዋል፡፡ሕልማቸውና የየንታ እውነቱ ፍቺ በምስክርነት ለትውልድ እንዲተላለፍ ፈቃዳቸው ለለነበረ ለተተኪ ተማሪዎቻቸው ሊናገሩ ችለዋል፡፡[15]

[15] ዘሆንታ አለቃ ማርቆስ ተማሪዎች አንዱ የነበሩት ሰው ጥሩ የመጽሐፍ መምህር ዘሚካኤል ፀሀይ በሐሴ ወር ፲፱፻፷፱ ዓ.ም የአባቴን ለቅሶ ለመድረስ አዲስ አበባ መጥተው በነበረው ጊዜ የመምህራቸውን ትእዛዝ ለመፈጸም ሲሉ ከላይ የተጠቀሰውን የአለቃ ማርቆስን ሕልም የነገሩን (ለሆንየንታ ማርቆስ ሕልም ከአባቴ ቃሉ ጋር ሲዛመድ እንዲሰጥ) አዲሱ ያሰቡት ግንኙነታቸው በመዝገብ ደምቀ ተቀርጾ ይገኛል፡፡



## ዲማና የጣልያን ወረራ ዘመን

በጣልያን ወረራ ዘመን አባቴ በዲማ ትምህርት ቤት ውስጥ ነበረ፡፡ በንባብ ቤት ውስጥ በቃል ትምህርት የጀመረው ትምህርት እየተቃናለት ሄዶ ንባብ፣ መዝሙረ ዳዊትና ዜማን አጠናቆ የቅኔ ትምህርት በመማር ላይ ነበር፡፡ ጠላት በሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶች እንዳደረገው ሁሉ ዲማንና አካቢውን በተደጋጋሚ በቦምብ ደብድቧል፡፡ ይህ የአውሮፕላን ድብደባ ከነሐሴ ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. እስከ መስከረም ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. ድረስ የዘለቀ ነው፡፡ በዚህ ተደጋጋሚ የቦምብ ድብደባ ታላቁንና ጥንታዊውን የዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳምን ለማቃጠል ሙከራ የተደረገ ቢሆንም በእግዚአብሔር ቸርነትና በሰማዕቱ ተራዳኢነት እንዳችም ጉልህ ጉዳት ሳይደርስበት በተአምር ሊጠበቅ ችሏል፡፡ ከ ፱ ቀናት በላይ በተፈጸመው ድብደባ የሞቱት ሰዎች ሦስት ናቸው፡፡

በጦርነቱ ዘመን ቀን ባንዳው፣ ሌሊት ሽፍታው አገሬውን ያስቸግር ነበር፡፡ የባንዳ፣ የሶልዳቶና የሐማሴን ቅልቅል[16] የነበረው ወራሪ የደበደበውን ደብድቦ፣ የቀማውን ቀምቶ፣ የዘረፈውን ዘርፎ ሲበላ ሲጠጣ ያድራል፡፡ ወራሪው ጦር ቀን በብዛት እየተሰማራ መድፍና መትረየስ ጠምዶ ሲደበድብ፣ ያገኘውን ሲዘርፍ፣ ሲበላ፣ ሲጠጣ ይውልና ማታ ተመልሶ ብቸና ከተማ ውስጥ ወደሚገኘው ካምፕ ገብቶ ያድራል፡፡ የማታው ተራ ደግሞ የሽፍታው ነበረ፡፡ አገሩ ዓባይ አፋፍ ላይ በመሆኑ ለሽፍታውም ለባንዳውም በጣም የተመቸ ነበር፡፡ የጦርነቱ ዘመን በተማሪ ቤቶች አካባቢ የተለየ ተጽዕኖ ነበረው፡፡

የጣሊያን ወታደሮች አንዳንዴ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ለሁለትና ለሦስት ቀን አዳር ባለአገሩ ውስጥ ገብተው ይሰፍራሉ፡፡ ሲመሽ ጠብቀው ወደ ተማሪ ቤቶች ይሄዱና በየጎጆው እየገቡ በተማሪዎቹ ፊት ላይ ባትሪ እያበሩ የሸሸጋችሁትን ሽፍታ አውጡ እያሉ በፍተሻ ስም ያንገላቷቸው ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ኮረብታማ ቦታ ላይ መድፍ

[16] ጥንቅ የሚባለው ከአገር ተወልዶ ተቀጥሮ ለፈረንጆቹ ወገን የሚሠራው ሲሆን ነው፤ ወታደሮቹ ባለአገሩ "ባንዳ" ይላቸው ነበር፡፡ ከሐማሴን ኢትዮጵያ አቅጣጫ ነው የተባሉ የበመተው ጀግና "ሐማሴን" ይባል ነበር፡፡

ጠምደው በከተማው ላይ እያሽጋገሩ ሲተኩሱ ይውሉ ነበር። የመድፉ ጩኸትና የእርሳሱ ፉጨት በተለይ ሕጻናትና ታዳጊ ተማሪዎች በጣም ያስጨንቃቸው ነበር። አባቴም ከነዚህ ተማሪዎች መካከል ይገኝ ነበረ።

በከተማው ውስጥ ተጠምደው የሚተኩሱት መሣሪያዎች ድምፅ ካሳደረበት ጭንቀት የተነሳ ባንድ ወቅት በቤተ ክርስቲያኑ አገልጋይ የነበሩትን አንዱን አዛውንት "አባባ አባክዎ ሆድዎ ውስጥ ደብቁኝ" እንዳላቸውና እርሳቸውም "እይ ልጄ ምን ሆዴ ቢተልቅ አንተን መያዝ የሚችል ይመስልሃል?" ብለው እየሳቁ አቅፈው እንዳባበሉት አጫውቶኛል። ለምን እንዲህ እንዳላቸው ሲጠይቀው ሆዳቸው በጣም ትልቅ ነው እየተባለ ሲወራ ይሰማ ስለ ነበር መሆኑን ነግሮኛል።

ዕለቱ ነሐሴ ፲፪ ቀን ፲፱፻፴፩ ዓም ነበር። በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን የሚፈጸም የቀብር ሥነ-ሥርዓት ስለ ነበረ በርከት ያሉ ሰዎች በቅጽር ግቢው ተሰብስበዋል። ወደ ዕቃ ቤቱ በሚወስደው መንገድ ላይ ከቤተ ክርስቲያኑ የሰሜን በር ፊት ለፊት ደግሞ እየተሯሯጡ የሚጫወቱ ታዳጊ ተማሪዎች ነበሩ። ከነዚህ ታዳጊዎች መሐል አባቴ ይገኝ ነበር። አዳነ ሙላቴ፥ አሰፋለና ባዩ ከተባሉ ጓደኞቹ ጋር በመሆን ከቁመታቸው በልጦ በተንዠረገገው አከርማና ሙርጅ[17] እየተሳሰሩ ለመጫወት ተስማሙና ጨዋታቸውን ቀጠሉ፤ትስስሮሹ ለእያንዳንዱ ተማሪ በተራ የሚደርስ ሲሆን ተረኛው ተማሪ በጀርባው ተንጋሎ እጆቹንና እግሮቹን በመስቀለኛ ቅርጽ ይዘረጋል። ከዚህ በኋላ የተዘረጉት እግሮቹ፥ እጆቹ እንዲሁም አንገትና ወገቡ በአከርማውና በሙርጁ ከመሬቱ ጋር ተጣብቀው ይታሰራሉ። ልጆቹ ከሚጫወቱበት ቦታ በቅርብ ርቀት ላይ በነበረ ትልቅ ድንጋይ ላይ ደግሞ ነጭ በነጭ የለበሱ አንድ ሰው ቆመው ዳዊት እየደገሙ ነበር። ሰውየው አቶ አየለ ጎይሉ የተባሉ በዚያን ሰሞን ከአዲስ አበባ ወደዚያው የሄዱ የአካባቢው ተወላጅ ነበሩ።

---

[17] ሙርጅ ወይም [illegible] በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ግቢ ውስጥ ከአከርማ ጋር [illegible] ነበረ።



ከቆሙበት ድንጋይ ግርጌ በሚጫወቱት ሕፃናት ጫጫታ የተረበሹት አቶ አየለ ጸሎታቸውን በመሐል በመሐል እያቋረጡ ለመገሠጽ ቢሞክሩም አልቻሉም። ልጆቹ ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ድምፃቸውን ለመቀነስ ይሞክሩና ጨዋታው ሲደምቅ ደግሞ የሰውየውን ቁጣ ረስተው እንደገና ይንጫጫሉ። የመታሰርና የመፈታቱ ተራ ለሁለት ልጆች ከተዳረሰ በኋላ በጨዋታው ሕግ መሠረት አባቴ በጀርባው ተዘርሮ መሬቱ ላይ ተኛ። በመስቀለኛ ቅርጽ የተዘረጉ እጆቹና እግሮቹ ወገቡና አንገቱ በአከርማና በሙርጅ ጠብቀው ታሰሩ። ወዲያው የጣሊያን የጦር አውሮፕላን ድንገት በአካባቢው ቦምብ ማዝነብ ጀመረ። በሁኔታው የደነገጡት ሦስቱ የአባቴ ጓደኞች እንደታሰረ ጥለውት ሸሹ።

የአቶ አየለ ጎይሉ ነጭ ልብስ በአካባቢው ሰው ለመኖሩ ምልክት ሰጪ ስለ ነበረ የአውሮፕላን አብራሪዎቹ ያንን ቦታ ዒላማ አደረጉት። ተከታትለው የተወረወሩት ቦምቦች አካባቢውን ሲያርሱት መሬቱ ተገለባበጠ። አቶ አየለም በቦምብ ተመቱ። አካላቸው በመቆራረጡ ከፊሉ ወደ እቃ ቤት ግቢ አቅጣጫ ተወርውሮ ሲወድቅ ከፊሉ ደግሞ አጠገባቸው በነበረው የዋንዛ ዛፍ ላይ ተንጠለጠለ። ቆመውበት የነበረው ድንጋይ ሳይቀር ተፈንቅሎ ከዕቃ ቤቱ ግቢ ውስጥ አረፈ።

ከመሬቱ ጋር ተጣብቆ የታሰረው አባቴ አውሮፕላን ሲመጣ ያዩ ሰዎች ሲፈፈሩና ሲሯሯጡ ከማዳመጥ ውጪ በማየት የሚገነዘበው ነገር አልነበረም። እየተፈጸመ ስለነበረው ጥፋት ለመገመትም ግንዛቤው አልነበረውም። መንቀሳቀስ በማይችልበት ሁኔታ ስለመታሰሩም ሆነ እንደ ጓደኞቹ ለማምለጥ ስለመቻል አለመቻሉ እንኳ ለማሰብ ጊዜ አልነበረውም። ራስጌው ቆመው ይጸልዩ በነበሩት ሰው አቅጣጫ የተወረወረው ቦምብ የተኛበትን መሬት ከገለባበጠው በኋላ ግን በማያየው የክረምት ሰማይ ሥር የሚዘንቡት የቦምብ አረሮች ምን እየሠሩ እንደ ነበረ ለማወቅም ሆነ አስደንጋጭ በሆነው የሞት ምስጥራዊ ግርማ ለመንቀጥቀጥ ግድ ሥጋዊ ዓይኖች አላስፈለጉትም ነበር። ፈራ፤ ተንቀጠቀጠ፤ ነገር ግን እንደ ጓደኞቹ ሮጦ ማምለጥ አልቻለም። በዚህም ምክንያት ያን ከመሰለ አደጋ ጋር ፊት ለፊት ተጋፈጠ። ቦምቡ ተወርውሮ፥ መሬቱ ተገለባብጦ፥ መሆን የነበረበት

ሁሉ ከሆነ በኋላ ከራስጌው የነበረው ግዑዝ ድንጋይና በላዩ ላይ ቆመው የነበሩት ሰው እንዳልነበሩ ሲሆኑ እሱ ግን በእግዚአብሔር ቸርነት ተረፈ፡፡ እጆቹ፣ እግሮቹ፣ ወገቡና አንገቱ የታሰሩባቸው እከርማና ሙርጅ ከሥር የተጣበቁበትን የአፈር ጓል እንደ ያዙ ከቀናው መሬት አካል ተላቀቁ፡፡

እጣብቆ ከያዘው የመሬት አካል መላቀቁን ሲገነዘብ እንደ ምንም ብሎ እየተውበረከረከ ተነሣና ከቀኝ እጁ ጋር የታሰረውን የአፈር ጓል እየጎተተ እግሩ ወደ ወሰደው አቅጣጫ ሮጠ፡፡ ከዚያም ወደ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ገባ፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ሰውነቱ በአፈር ብናኝ ከመሸፈኑ ሌላ ምንም ዐይነት የቁስለትም ሆነ ጭረት ምልክት አልነበረውም፡፡ አባቴ ተንጋሎበት በነበረበት ቦታ ላይ የሆነውን ያየ ሁሉ የእርሱን በሕይወት መትረፍ ሲመለከት እጅግ አድርጎ ተደነቀ፡፡አውሮፕላኖቹ የዕለቱን ድብደባ አጠናቀው ተመለሱ፡፡ በአደጋው የሰው ሕይወት በመጥፋቱና በተከታታይ ቀናትም ሊከተል የሚችለውን አደጋ በመሥጋት የአገሬው ሰው በጭንቀትና በኀዘን ዋለ፡፡ ከመኖሪያ አካባቢዎች ይልቅ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ መሸሸጉ አደጋውን ይቀንሰዋል የሚል እምነት ስለ ነበረ ብዙ ሰዎች በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽረ ግቢ ውስጥ ተደብቀው አደሩ፡፡ በማግስቱም ምክር ያዙ፡፡ ከፊሉ ሰው ወደ ዋሻ፣ የተቀረው ወደ በረሀ አንዳንዱ ደግሞ ወደ አውራጃው ዋና ከተማ እንሂድ እያሉ ሲከራከሩ በአንድ ሐሳብ ሳይቆርጡ ሰዓቱ ረፈደ፡፡  የጠላት ድብደባ እንደገና ጀመረ፡፡ በዚህ ዕለት ቦምብ ሲወረውሩ የነበሩት አውሮፕላኖች ብዛት ስድስት ሲሆን ሕዝቡ በየዋሻው በመደበቁ የሰው ሕይወት አልጠፋም፡፡ ባለፈው ቀን የተፈጠረው አደጋ የሞቱት የአቶ አየለ ቀብርም የተፈጸመው በከፍተኛ ጥንቃቄና ፍርሃት ነበረ፡፡

በጠላት ዘመን የአባቴ እናት የሚኖሩት ጠልማ ከሚባል አካባቢ ነበር፡፡ ከጎረቤቶቻቸው መሐል የአቶ አየለ ኃይሉ የቀብር ሥነ-ሥርዓት ላይ ተገኝተው ማምሻውን ወደ ሀገራቸው የተመለሱ ሰዎች ነበሩ፡፡ ስለ እጋጠማቸው የቦምብ ድብደባ፣ ሰላዩትና ስለ ሰሙት ሲያወሩ እያቴ እሞኘሽ እምባዬ ከወሬው መሐል የልጃቸው ስም ሲጠራ ሰሙ፡፡ "...እግዚአብሔር ዕድሜውን ያልቆረጠው አይሞትም፡፡ አየለ ኃይሉ



ሲሞት የታምሩ የተመኘ ልጅ መትረፉ ይገርማል፡፡..." እየተባለ ስለ ራሳቸው ልጅ ሲወራ ሰሙ፡፡ በሰሙት ወሬ የተደናገጡት እያቴ ሌሊቱን በጭንቀትካሳለፉ በኋላ በማግስቱ ወደ ዲማ ሄዱ፡፡

በዚያ አካባቢ የነበረው የጠላት ጥቃት እየተጠናከረ መምጣቱ የሕዝቡን በተለይም ከቤተሰብ እርቀው በቤተ ክርስቲያን እርዳታ ብቻ የሚኖሩትን ተማሪዎች ሕይወት የሚፈታተን ስለ ነበር እሞኘሽ እምባዬ ልጃቸውን ራቅ ወዳለ ስፍራ ለማሸሸ ወሰኑ፡፡ በዚህ ውሳኔያቸው መነሻነትም ናብራ ወደሚባል አገር ይዘውት ሄዱ፡፡ ናብራ የሚባለው አገር ባንዶች የሰፈሩበት ስለ ነበረ በጊዜው ምንም ዓይነት የፀጥታ ሥጋትና ችግር አልነበረበትም፡፡ አባቴ ወደ ናብራ ያደረገው ጉዞ ከዲማ ውጪ የነበረውን የትምህርት ሕይወት ያየበት የመጀመሪያ ጉዞው ነበር፡፡

# የመንግሥቶ ቅኔ ቤት

እናቱ ወደ ናብራ ካደረሱት በኋላ መንግሥቶ ይገኙ ከነበሩት የቅኔ መምህር ከየኔታ ያሬድ ጉባኤ ዘንድ ገባ፡፡ መንግሥቶ የሚገኘው በብቸና አውራጃ በእነማይ ወረዳ ጀራሹም በሚባለው ቦታ ሱሀና የበርት ከሚባሉት ወንዞች መሐል ነው፡፡ በመንግሥቶ የሚገኘው ቅኔ ቤት በዛን ጊዜ ከነበሩት ታዋቂ የቅኔ ትምሕርት ቤቶች አንዱ ነበር፡፡

አባቴ ዲማ ሳለ የዜማ ትምህርቱን በበቂ ሁኔታ ያጠናቀቀ ቢሆንም ወደ ቀጣዩ ትምህርት አልገባም፡፡ የቀድሞ ተማሪዎች ከአንዱ መምህር የተማሩትን ከሌላ ታዋቂ መምህር ዘንድ ሄደው ማደላደልና ራሳቸውን መፈተን የሚወዱ ስለነበሩ ወደ መንግሥቶ በሄደ ጊዜ መጀመሪያ የገባው ወደ ዜማ ትምሕርት ቤት ነው፡፡ በዜማ ትምሕርት ቤት ውስጥ ርቀት ካለው ቦታ የመጡ ብዙ ተማሪዎች አልነበሩም፡፡ የሚበዙት ተማሪዎች የአካባቢው ተወላጆች በመሆናቸውና የሚማሩትም በተመላላሽነት በመሆኑ ቅርርባቸው ከቤተሰቦቻቸውና ከአካባቢ ጓደኞቻቸው ጋር ብቻ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት እንደ እኔ አባት ከሩቅ ቦታ ሄዶ ለሚማር ተማሪ የዕለት ቀለቡን ዞሮ መለመንም ሆነ ምግብ የሚያካፍል ጓደኛ ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡

አባቴ የዕለት ቀለቡን በተመለከተ ከዲማ ቀጥሎ ለሁለተኛ ጊዜ በጣም የተቸገረው በዜማ ቤት ቆይታው ነው፡፡ በትምሕርት ቤት ዓለም ለመጀመሪያም ለመጨረሻም ጊዜ አኩፋዳና በትር ይዞ መንደር ለመንደር እየተዘዋወረ "በአንተ ስማ ለማርያም" እያለ የዕለት ምግቡን የለመነበት ቦታም መንግሥቶ ነው፡፡ መንግሥቶ የገብስ አገር በመሆኑ የበሰለ ምግብ የሚመጸውተው ባጣ ጊዜ እንዲጠቅመው በማሰብ በመኸር ጊዜ ከአውድማ ገብስ ለምኖ ያስቀምጥ ነበረ፡፡ ቁራሽ የሚዘከረው ባጣ ቀን ከዚያ ካስቀመጠው ገብስ አስቆልቶ ይመገብ ነበር፡፡ የዕለት ቀለቡን ነገር በዚህ ሁኔታ እያስታመመ በመንግሥቶ ዜማ ቤት ያደረገውን አጭር ቆይታ አጠናቆ ወደ ቅኔ ቤት ገባ፡፡



የቅኔ ቤት እንደ አሁኑ ዘመን ኮሌጆች ወይም ዩኒቨርስቲዎች ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የመጡ ተማሪዎች የሚሰበሰቡበት ቦታ መሆኑን አባቴ ነግሮኛል፡፡ በመንግሥቶ ቅኔ ቤት ከሸዋ፣ ከጐንደር፣ ከትግራይ፣ ከወሎ እና ከሌሎችም የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር የመጡ ተማሪዎች ይገኙ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት አባቴ በቅኔ ቤት ብዙ ጓደኞችን የማፍራት ዕድል ገጠመው፡፡ ቅኔን ዲማ ቆይሮ ስለ መጣና በአእምሮው ብሩህነት ምክንያት ከሌሎች የተሻለ ችሎታ በማሳየቱ በትምህርታቸው ደከም የሚሉትንና ጀማሪዎችን ያስጠና ነበር፡፡ ልክ እንደ ዲማ ሁሉ እዚያም ብዛት ያላቸው ተማሪዎች ይከቡት ነበረ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በማይጨው ዘመቻ ወቅት ለሀገራቸው ድንበርና ለወገናቸው ክብር ለመዋጋት ወጥተው ጣልያን ድል ሲያደርግ "ተመልሰን ሀገራችን እንገባም" እያሉ በምናኔ መልክ የቀሩ ብዙ መኳንንት በተማሪዎቹ መሐል ይገኙ ነበር፡፡ እነዚህ ጐልማሳ ተማሪዎች ከመደበኛዎቹ ሕፃናት ተማሪዎች በዕድሜ በጣም የሚበልጡ ከመሆናቸው በተጨማሪ ትምህርት የመቀበል ፍጥነትና ችሎታቸው ከሕፃናቱ ጋር የሚመጣጠን ስላልነበረ ትምህርቱን እኩል ለመሳተፍ ይቸገሩ ነበረ፡፡ ለመጠየቅም ያፍሩ ነበረ፡፡ አባቴ እንደዚህ ዐይነቶቹን ሰዎች ከመደበኛ የትምህርት ሰዓት ውጪ በማስጠናትና ለጥያቄዎቻቸውም መልስ በመስጠት ይረዳቸው ነበረ፡፡ እነርሱ ደግሞ በአጠፌታው ከሚለምኑት የዕለት ምግብ ያካፍሉት ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት በዜማ ትምህርት ቤት ከገጠመው የምግብ ችግር ተላቀቀ፡፡ ማታም ሆነ ጠዋት እነሱ የፈለጉትን ያህል ያስጠናቸዋል፡፡ ጥያቄዎቻቸውም መልስይሰጣቸዋል፡፡የተማረውንማስተማርን ወይም ለሌሎች ማካፈልን ገና በዚያ ቢጋ ዕድሜው እግዚአብሔር ዕድል አድርጎ ሰለ ሰጠው በዚሁ እየተረዳ ብዙ ጊዜ ቆየ፡፡ ከዚያም በቅኔ መምህርነት ተመረቀ፡፡

# ሸግሸጎ መድኃኔ ዓለም እና የተስቦ በሽታ ፈተና

አባቴ በቅኔ መምህርነት ከተመረቀ በኋላ ከየኔታ መምህር ያሬድ በታች በራፊ ሆነ፡፡ በዕለታዊው የትምህርት ሂደት ውስጥ የኔታ ያሬድ ለሥርዓቱ አንድ ጊዜ ይገኛሉ እንጂ ከዚያ በተረፈ ተማሪውን የሚያስተናግደው እርሱ ነበረ፡፡ ምንም እንኳን በዕድሜ አነስተኛ ቢሆንም በደረጃው ግን ከመምህሩ ከየኔታ ያሬድ ቀጥሎ የሚገኘው እሱ ስለ ነበረ የተማሪዎቹን ችግር የሚያዳምጥ፣ የሚመክር፣ ቢጣሉ የሚያስታርቅ አንዳንድ ሐሳቦቻቸውንም ለመምህሩ ያቀርብ እሱ ነበረ፡፡ በሥሩ የሚማሩት ተማሪዎች ኀበዞች እንዲሆኑ የማበረታታትና የማደፋፈር የሚያውቀውንም ሁሉ ያለ ምንም ስስት የማስረዳት ልዩ የሆነ ተሰጥዖም ነበረው፡፡

በአንድ ወቅት የኔታ ያሬድ ጠበል ለመጠመቅ ሸግሸጎ መድኃኔ ዓለም ወደሚባል ቦታ ሄዱ፡፡ ሸግሸጎ መድኃኔ ዓለም የሚገኘው ወደ ሸዋ ምላሽ ደጀን አጠገብ ነው፡፡ አባቴና ሌሎቹ ተማሪዎች መምህራቸውን የኔታ ያሬድን ተከትለው ወደ ሸግሸጎ መድኃኔ ዓለም በመሄዳቸው ዕለታዊ የመማር ማስተማር ሂደቱ ቀጠለ፡፡

በሸግሸጉ መድኃኔ ዓለም የነበሩ ተማሪዎች ለዓመት ልብሳቸው መግዣያ ገንዘብ የሚያገኙት ቆርኪያ ሰብስበው ወደ ወሎ በመሻገር በደበሎ እየለወጡ ነበር፡፡ ቆርኪያው የሚፈለገው የእንዝርት[18] ዛቢያ ለመሥራት ሲሆን ተማሪዎች ደግሞ በልዋጩ የሚያገኙትን ደበሎ እየሰፉ ልብስ ያደርጉ ነበር፡፡ በዚሁ ልማድ መሠረት ከሚመላለሱት ተማሪዎች መሐል አዳሙ የሚባል የሞጣ ልጅ ቆርኪያ ሊያመጣ ደጋ ሄዶ ሲመለስ የተስቦ በሽታ ገብቶ ከወጣበት ቤት አድሮ ኖሮ በሽታ ይዞ መጣ፡፡ በጣምም ታመመ፡፡ "ይሄ አማረኝ ... ያ አማረኝ..." ማለት ሲጀምር ብዙዎቹ ተማሪዎች በተስቦ በሽታ ላለመያዝ ሽሽት ጀመሩ፡፡

[18]ሴቶች ጥጥን ወደ ክር [illegible] የሚጠቀሙበትን የፈትል ሥራ [illegible] እንዝርት ይባላል፡፡ እንዝርት [illegible]



የተስቦ በሽታን ከመፍራት የተነሳ ጤነኛ ሰዎች የታመሙትን በመርዳት ፋንታ ይሸሿቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት አዳሙ ሲታመም ካሣ የሚባል አንድ ጓደኛው ብቻ አብሮት ሲቀር ሌሎቹ ጥለውት ሸሹ፡፡ አስታማሚውና እሱ በአንድላይ መኖር ስለማይችሉ ለብቻው ተገልሎ የሚተኛበትን አዲስ ጎጆ መሥራት አስፈላጊ ነበረ፡፡ አባቴና የበሽተኛው ጓደኛ ካሣ ከትልልቆቹ ተማሪዎች ጋር በመተጋገዝ ከሠሩለት በኋላ በዚያ ተኝቶ እንዲታመም አደረጉ፡፡

አባቴ ከቀለም ትምህርቱ በተጨማሪ የተማራቸው የሙያ ክህሎቶች ነበሩት፡፡ ከነዚህ መሐል የታሸ ቆዳ አስተካክሎ የተማሪዎችን ደበሎ መስፋት፣ እጀ ጠባብና ሱሪ መስፋት፣ እንዲሁም ድርብና ነጠላ ስሌን የመስራት ችሎታ ነበረው፡፡ እነዚህን ሠርቶ በመሸጥ በሚያገኘው ገንዘብ የዓመት ልብሱን ይገዛ ነበር፡፡ የተማሪ ኑሮ ማኅበራዊ እንደ መሆኑ መጠን የተማሪ ጎጆዎች በሚሠሩበት ጊዜ ማገር የሚታሰርበትን ልጥ በማዘጋጀት እንጨት በማቀበልና በመሳሰሉት ሥራዎች ላይ በንቃት ይሳተፍ ነበር፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን አባቴ በሽተኛውን አዳሙን ለመጠየቅ ሲገባ የተልባ ፍትፍት እንዳማረው በማስተዛዘን ነገረው፡፡ ከየትም ብሎ ፈልጎ እንዲያመጣለትም ጠየቀው፡፡ ተማሪዎች በሙሉ ሸሽተው ስለ ነበረ የሚላክ ሰው አልነበረም፡፡ ስለዚህ እሱ ወደ መንደር ወርዶ ፈልጎ አመጣለት፡፡ ምግቡን ለማምጣት ሲሄድም ሲመለስም ኃይለኛ የቀትር ፀሐይ መታው፡፡ ያመጣውን ምግብ ለአዳሙ ሰጥቶ ከተመለሰ ሰዓት ጀምሮ የሕመም ስሜት ተሰማው፡፡ የፀሐዩ ግለትና የምግቡ ሽታ ተደባልቆ እንዳች ዓይነት የጤና ሁከት ፈጠረበትና በዘልማድ "ምች" እየተባለ የሚጠራው ሕመም አገኘው፡፡ ከዚያም በተጨማሪ ተስቦው ወደ እርሱ ዞሮ በጠና ታመመ፡፡ ይህ ሕመም የጀመረው ሐምሌ ፳ ቀን ሲሆን እስከ ነሐሴ ፲፮ ቀን ድረስ ያለበትን ቦታ ሳያውቅ ታሞ ሰነበተ፡፡ ምግብ ሳይበላ ውሃ ብቻ እየጠጣ እንደ ሰነበተ ከአስታማሚው ከካሣ የተነገረውን መሠረት በማድረግ ነግሮኛል፡፡

በዕድሜው ታናሽ ስለ መሆኑ፥ ስለ ዐቅሙ ማነስ፥ ስለ ዓይነ ሥውርነቱም ጭምር እያሰቡ ለአባቴ የሚያዝኑለትና የሚደግፉት የደብሩ አቃቢት ነበሩ። እኚህ ሴት የነሐሴ ኪዳነ ምሕረትን በዓል የመዘከር ልማድ ነበራቸው። በዚሁ ቀን የተለመደውን ዝክር በሚያደርጉበት ወቅት አባቴን አስታውሰውት ኖሮ የሚቀምሰው ጸዲቅ ይዘው ሊጠይቁት መጡ። ዘወትር ስለርሱ ከሚሰማቸው ርኅራኄ በተጨማሪ የህመሙ ክብደት ያስከተለበት ከፍተኛ ጉዳት ደግሞ ይበልጥ ስላሳዘናቸው በጣም አለቀሱ። እንደ ምንም አባብለውት ከያዙት ምግብ ጥቂት ካጐረሱት በኋላ ተመልሰው ሄዱ። ያንን ጸዲቅ ከቀመሰ በኋላም ተመልሶ ተኛ። ያኔ የተኛ በማግሥቱ በተመሳሳይ ሰዓት ከዕንቅልፉ ነቃ።

በግምት ከሃያ አራት ሰዓታት ላላነሰ ጊዜ ከወደቀበት እንቅልፍ ሲነቃ ከአስራ አምስት ቀናት በኋላ የመጀመሪያው የሆነው ረኀብ ስሜት ተሰማው። ከአጠገቡ ሳይለዩ ሲያስታምሙት የነበሩት ትእዛዙ የሚባል የደጋ ዳሞት ተወላጅና ገብረ ሥላሴ የሚባል የአምባሰል ተወላጅ ጓደኞች ነበሩት። ከእንቅልፉ ነቅቶ ምግብ የሚያቀብለው ሰው ሲጣራ እነዚህ ጓደኞቹ ዐቃቢቷ ካመጡለት ምግብ የተረፈውን አስቀምጠውለት ኖሮ ከዚያው ላይ ቀንሰው ሰጡት። በዚያ ጊዜ ስለ ነበረው ሁኔታ በሰጠው አንድ ቃለ መጠይቅ ላይ እንደተናገረው "... ያቺን እንጀራ እየቀነሰኩ... እየቀነስኩ ሰበላ ስበላ አንድ እንጀራ ለሁለት ቀን ሆነችኝ..." በማለት ገልጦታል። ከዚያ ቀን በኋላ የመዳን ምልክት እያሳየ ከቀን ወደ ቀንም እየጠነከረ ለመነሣትና ለመንቀሳቀስ ሙከራ ማድረግ ጀመረ።

አባቴ እንደ ነገረኝ የተስቦ በሽታ ከሚያስከትላቸው ፈተናዎች አንዱ ታመው ከዳኑ በኋላ የሚከተለው ረሀብ ነው። ታላቅ የረሀብ ፈተና አለበት። በዚሁ ምክንያት እሱም ከዳኑ በኋላ ከዚህ ፈተና ማምለጥ አልቻለም። በጣም ይርበው ጀመር። ተስቦ የያዘው ሰው ሲድን በአካባቢው ጠዳለ ሰው ይጋባል የሚባል ሥጋት ስለ ነበረ ይህን በመፍራት ሲያስታምሙት የነበሩ ጓደኞቹን አስናበታቸው። አስታማሚዎቹ ሲሄዱ በዚያ ቦታ የቀሩት እሱና እንደ እሱ ታመው የዳኑ ሌሎች ሁለት ተማሪዎች ብቻ ነበሩ።



ተማሪዎቹ ምንም ቢድኑም ሕመሙ በጣም ጎድቷቸው ስለ ነበረ እንደልብ ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የሚችሉበት ዐቅም አልነበራቸውም። ከዚህም በተጨማሪ መልካቸው በጣም ገርጥቶ ነጭ ሆነው ስለ ነበረ ለልመና ወደ መንደር ሲወጡ ሰው ሁሉ እየፈራ ይሸሻቸው ነበር። ገመምተኞቹ ተማሪዎች ለበሥራ አምስት ቀናት ያህል ከባድ የረኀብ ፈተና ከተጋፈጡ በኋላ ያለ የሌለ ኃይላቸውን አሰባስበው ወደ መንግሥቶ ለመመለስ ተነሡ። በጤንነታቸው ጊዜ በአንድ ቀን ያጠናቅቁት የነበረው ይህ መንገድ በዚያ ጊዜ ግን ሦስት ቀን ፈጀባቸው። ከአባቴ ጋር የተጓዙት ሁለት ሰዎች ከመንግሥቶ በኋላ ጉዞአቸውን ወደ ሌላ አገር ሲቀጥሉ እርሱ ግን በጣም ስለ ደከመው እዚያው ቀረ።

መንግሥቶ ሲደርስ ደግሞ ሌላ ፈተና አጋጠመው። ያ ከሸግሸጉ መድኃኔ ዓለም ያሳደደው ተስቦ ከመንግሥቶ የተማሪዎች መንደር ገብቶ ብዙ ሰው ገድሎ ኖሮ የበረቱት ሸሽተው፤ በዐቅም ማጣት የተነሣ በዚያው የቀሩ ሦስት ተማሪዎች ብቻ አገኘ። ከእነርሱ ሁለቱ ታመው አንዱ ደግሞ አስታማሚ ሆኖ ነበር። ይህ አስታማሚ ቀደም ብሎ ከሚያስታምማቸው በሽተኞች በተጨማሪ ሌላ ሰው ጨምሮ ለመርዳት የሚያስችል ዐቅም አልነበረውም። መረዳዳቱን ከሁሉ በላይ ከባድ የሚያደርገው ደግሞ በተለይ ምግብ እንደ ልብ አለመገኘቱ ነበረ።

የመንግሥቶ ትምሕርት ቤት የሚገኝበት ቦታ ተራራማ ሲሆን የአካባቢው ሰው የሚኖርበት ሰፈር ደግሞ ከተራራው ሥር ነበረ። በዚህ ምክንያት በህመም የተዳከመ አቅም ለነበራቸው ተማሪዎች ወደ መንደር ወርዶ መለመን ፈጽሞ የማይታሰብ ነበር። ስለዚህ አባቴ ያለምንም ረዳት በተራራው ላይ ውሎ ከማደር በቀር ሌላ አማራጭ አላገኘም። በመሆኑም በረኀብ ላለመሞትና በሕይወት ለመቆየት የሚያስችለውን መንገድ መፈለግ ነበረበት። ይህንን እያሰላሰለ ሳለ ውጥንቅጥ እኽል የሚቀመጥባት የሸምበቆ ቀፎ ትዝ አለችው። በጊዜው በነበረው ልማድ መሠረት ተማሪዎች ሲለምኑ ጥሬ እኽል ከተሰጣቸው ያገኙትን ጥሬ በሙሉ አንዱን ከአንዱ ሳይለዩ በሸንበቆ ቀፎ ውስጥ

ያጠራቅማሉ፡፡ ገብሱም፣ ሰንዴውም፣ ባቄላውም ፣ሽምብራውም፣ ጓያውም፣ ምስሩም፣ ከጤፍ በስተቀር የተገኘ የእኽል ዘር ሁሉ በቀፎው ውስጥ ይቀመጣል፡፡ የሚኖሩበት ቦታ በክረምት ዙሪያውን በውሃ ስለሚከበብ ወደ መንደር ሄደው ለመለመን የሚችሉበት መንገድ አልነበራቸውም፡፡ ስለዚህ ያንን ያጠራቀሙትን ውጥንቅጥ እኽል የሚርሰውን እያራሱ፣ የሚቆላውን እየቆሉ፣ የሚቀቀለውን እየቀቀሉ ሲመገቡ ይከርማሉ፡፡

ከተሰቦ ሕመም ገና በማገገም ላይ የነበረው አባቴ ከዚያ ተራራማ ቦታ መውጪያ ዕድል ስላልነበረው የመጨረሻ ተስፋው ሆና የተገኘችው በጎጆው ውስጥ የነበረችው የሣር ቀፎ ብቻ ነበረች፡፡ በቀፎ ውስጥ የነበረውን ቅይጥ ጥሬ የሚቆላለት ወይም የሚቀቅልለት ሰው አልነበረምና ያልበሰለውን ጥሬ ለመብላት መሞከር ነበረበት፡፡ እንደዚያ ለማድረግ ደግሞ በየጊዜው ቀፎ ብድግ እያለ ቀፎውን ማውረድ ማውጣት አስፈላጊ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ይህን ለማድረግ የሚያስችል ጥንካሬና ጉልበት ስላልነበረው አሁንም ሌላ ዘዴ መፈለግ ነበረበት፡፡ ስለዚህ እንደ ምንም ብሎ ቀፎዋን ከሥር በእንጨት ከበሳት በኋላ እንደ ከዳን እንዲያገለግል የጨርቅ ቁራጭ አበጀላት። በዚያው አንጻር ደግሞ ከታች ሆኖ የሚፈሰውን ጥሬ የሚቀበልበት እንደ ጎድጓዳ ሣህን ያለች የእንጨት ገበቴ ደቀነ፡፡ የሚበላውን ጥሬ በሚፈልግ ሰዓት ያቺን የከደናትን ጨርቅ ይከፍታታል ከዚያም ጥሬው ወደ ተደቀነው የእንጨት ገበቴ ይፈሳል፡፡ የሚፈልገውን ካገኘ በኋላ ደግሞ መልሶ ያዘጋጀውን የጨርቅ ቁራጭ ይወትፈዋል፡፡ የፀሐይ ሙቀት ይናፍቀው ስለ ነበረ ያጠራቀመውን ጥሬና አጐዛውን ይይዝና እንደ ምንም እየተንገዳገደ ወደ ውጪ ይወጣል፡፡ ከዚያም ከአጐዛው ላይ ጋደም ብሎ ሽምብራ ሽምብራውን ብቻ እየለቀመ ይበላል፡፡ ሰንዴውን፣ ገብሱንና ባቄላውን ለመቆርጠም ጥርሱ ስለማይችልለት እየመረጠ ይተወዉ ነበር፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ መስከረምና ጥቅምት ፲፱፻፴፫ ዓመተ ምሕረትን እንደምንም ብሎ ዘለቀ፡፡



እንግሊዞችና ደጃዝማች በላይ ዘለቀ መንግሥቶ ላይ በተወያዩበት ሳምንት ውስጥ[19] እንዱን ቀን አባቴ ወደ ነበረበት ቤት አባ ጎፋይ የተባሉ ድንገተኛ እንግዳ መጡ፡፡ አባ ጎፋይ እዚያ መንግሥቶ ተማሪ የነበሩ መነኩሴ ሲሆኑ በሽታው በገባ ጊዜ የሸሹ ነበሩ፡፡ ነገር ግን የተሰቦን መዘዝ በሄዱበትም ሊያመልጡት ባለመቻላቸው ታመሙ፡፡ በዚህን ጊዜ ጓደኞቻቸው ጨለማን ተገን አድርገው ወደ መንግሥቶ መልሰው አምጥተው አባቴ ከነበረበት ቤት በር ላይ ጥለዋቸው ሄዱ፡፡ አባ ጎፋይ በሽታው ብዙ አልጠናባቸው ኖሮ ቶሎ ተሻላቸው፡፡ አባቴም ጓደኛ ሲያገኝ ተበረታታ፡፡ ሁለቱ ገመምተኞች እየተደጋገፉ ራሳቸውን ለማጠናከር ይፍጨረጨሩ ጀመር፡፡

ኅዳር የእሸትና የመኸር ወር በመሆኑ ለጐጃም ተማሪ በጣም የተመቸ ወቅት ነው፡፡ እንደ ቊስቋም፣ ቅድስት ሃና፣ ቅዱስ ሚካኤልና ጽዮን ማርያምን የመሳሰሉ ሃይማኖታዊ በዓላት በተከታታይ የሚዘከሩበት በመሆኑ አባቴና አባ ጎፋይም ከየዝክሩ የሚያገኙትን እየተመገቡ ተበረታቱ፡፡ እኽል የማይጠግነው የለምና ከዚያ በኋላ እንደ ምንም ብሰው እየበረቱ ሄዱ፡፡ በሽግሽጉ መድኃኔ ዓለም ተጀምሮ መንግሥቶ ያበቃው የደዌ ፈተና በአባቴ ሕይወት ውስጥ የማይረሳ ትዝታ ጥሎ አልፏል፡፡ በዲማ ቆይታው የተጐዳው የልጅነት ሰውነቱ የተሰቦ በሽታና የረኅብ ፈተና ሲጨመርበት ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ ጎድቶት ነበር፡፡

ህንንም በማስታወስ በ፲፱፻፹፭ ዓ.ም ለአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ የአማርኛ ክፍል በሰጠው ቃለ መጠይቅ ላይ "… ይሄ ምን ጊዜም አይረሳኝም፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሰውነቴና ጤንነቴ ሊስተካከል አልቻለም፡፡ ቢሆንም በትምህርቴ ላይ ያን ያህል ለውጥ አላመጣም…" በማለት ገልጾታል፡፡

ከ ፲፱፻፳፯ እስከ ፲፱፻፴፯ ዓ.ም. በዘለቁት አስር ዓመታት ውስጥ አባቴ በንባብ ቤት፣ በዜማ ቤትና በቅኔ ቤት የሚሰጡትን ትምህርቶች አጠናቅቆ በቅኔ መምህርነት ቍመርቋል፡፡ ከመንግሥቶ ወደ ዲማ ከሄደ

[19] በዚያን ወቅት "ጃንሆይ ሊመጡ ነው" እየተባለ ወሬ ከየአቅጣጫው በመናፈሱ ላይ ሰለነበረ እንግሊዞችም በየአካባቢው እየተዘዋወሩ የሸፍቶችን በዙት ይቃኙ ነበር። በዚህ መሠረት ደጃዝማች በላይ ዘለቀ የእንግሊዝን መልእክተኛ ያነጋገሩት ጥቅምት ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ቢሆን በታወቀም የመንግሥት ትምሕርት ቤት ከነበረበት ተራራ ግርጌ ባለው ሜዳ ላይ ነበር።

በኋላ ወደ ዜማ ትምህርት ቤት ተመልሶ ጸዋተወ ዜማን ከመምህር እልማውና ከመሪጌታ ክንፉ ፍትሐ እምባክ ተምሯል፡፡ከዚያም ከየንታ እልማው ዘንድ አቋቋም ተምሯል፡፡ እኒህ ታላቅ ሊቅና መንፈሳዊ አባት፣"አገልግሌን ይዘህ ወደ ሩቅ አገር ስትሄድ በሕልሜ አይቻለሁ፡፡ አገልግሎትህ ለሩቅ አገር ነው እንጂ ለዲማ አይደለም፡፡ "በማለት ለዲማ ከነበራቸው ፍቅር የተነሣ እዚያው ኖሮ ገዳሙን ላያገለግል ምን አደከመኝ በሚል መንፈስ ከትምህርቱ አገዱት፡፡

እሱ ደግሞ ተስፋ ቆርጦ በመራቅ ፈንታ ልክ በልጅነት ዕድሜው ያደርግ እንደ ነበረው ሁሉ በእብሮ አደግ ጓደኛው መሪጌታ እውነቴ እግዛ ማታ ማታ ዐብሮ ማጥናት ጀመረ፡፡ ይህ ጥረቱ ተሳክቶለት ያሳየው የዕውቀት ብቃት ብዙዎችን አስገረመ፡፡ ይህንንም መምህሩ ሰሙ፡፡ ቁርጠኝነቱ፣ ጥረቱ፣ ጥንካሬውና ችሎታው ያስደነቃቸው መምህር እልማው "ልጄ እግዚአብሔር ያልከለከለህን እኔ ልከለክልህ አልችልም"ብለው ወደ ጉባኤያቸው ገብቶ መማሩን እንዲቀጥል ፈቀዱለት፡፡ ከዚህም አልፈው ተርፈው እርሳቸውን ለመጠየቅ የሚመጡ ሰዎች የሚያመጡላቸውን ምግብ ለአባቴና ለመሪጌታ እውነቴ እያካፈሉ የምግብ ድጋፍም ያደርጉላቸው ጀመር፡፡

ከየንታ እልማው ዘንድ ይማር የነበረውን የአቋቋም ትምህርት አጠናቅቆ በመምህርነት ከተመረቀ በኋላ ወደ ትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርት ቤት ገባ፡፡ በዚያም የመዝሙረ ዳዊትን ትርጓሜ ከመምህር እጅጉ ቸሬ፥ ብሉያትንና የመጽሐፈ ነገሥትን ከመምህር አካሉ ተማረ፡፡ በመቀጠልም ከጓደኛው ከመሪጌታ እውነቴ ጋር በመሆን የውሽ ወደሚባለው አገር ሄደው ከታወቁት የዜማ መምህር ከየንታ መምህር እውነቴ ዘንድ የዜማ ትምህርቱን አስመሰከረ፡፡ ከየውሽ እንደገና ወደ ዲማ በመመለስ የትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርቱን ቀጥሎ ሐዲሳትን፥ መጽሐፈ ሊቃውንትንና መጽሐፈ መነኮሳትን ተማረ፡፡

አባቴ በአንድ ዓይነት ትምህርት ላይ ብቻ ራስን መወሰን አይገባም የሚል እምነት ነበረው፡፡ ይኼ እምነቱ ከልጅነት እስከ አረጋዊነት ዕድሜው ድረስ ፀብሮት የዘለቀ ነው፡፡ በተለይ በልጅነትና በወጣትነት



ዘመኑ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከምትሰጣቸው ትምህርቶች በአንዱም ጎድሎ ላለመገኘት ይጣጣር ነበር፡፡ በመሆኑም ባደረገው ጥረት ዐቅምና ሁኔታ የፈቀደለትን ያህል ለመገብየት ችሏል፡፡ ስለ ትምህርቱ ከአሜሪካ ድምጽ የአማርኛ ሬዲዮ ለቀረበለት ጥያቄምከዚህ በታች የሠፈረውን መልስ ሰጥቷል፡፡

"... ትምህርት ቤት የገባሁት በ፲፱፻፳፭ዓ.ም. ወይም፲፱፻፳፮ ዓ.ም.ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወደ ቤተሰቦቼም አልተመለስኩም፡፡ ጠቅላላ ህይወቴን ከተማሪዎች ጋር ነው የኖርኩት፡፡...መጀመሪያ ንባብ፣ መዝሙረ ዳዊት፣ ከዚያም ቀጥሎ ዜማ፣ ቅኔ፣ ትርጓሜ መጻህፍት፣ አቋቋም...በቤተክርስቲያን ሙያዎች የሚቀመሰውን ሁሉ በጊዜው ሞክሬአለሁ፡፡አንድ ሀሳብ የነበረኝ ከልጅነቴ ጀምሮ ደካማነቴን አውቃለሁ፡፡ አንዱ ነገር ቢጐድል፤ ምናልባት እግዜአብሔር ዕድሌንና መተዳደሪያዬን በዚያ በኩል ካደረገው፣ያንን ሳላውቀው ከቀረሁኝ በምን እረዳለሁ? የሚል ሀሳብ ነበረኝ፡፡ እርሼ ቆፍሬ እራሴን መርዳት የማልችል ነኝና በቤተክርስቲያን ባለው ሙያ ግን ቢያንስም ቢበዛም፤ ሊሆን ስሰው የምተርፈው ብሆን፤ ቢታጣ እንኳን በቤተክርስቲያን አገልግሎት ተሳትፎ ሙሉነት እንዲኖረኝ እጥር ስለነበረ ሁሉም የቤተክርስቲያን ሙያዎች ሞክሬአለሁ፡፡"በተጨማሪም በየዘርፉ ለገበየው ዕውቀት ሁሉ መሠረታዊ ትምህርትን ያገኘው በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከነበሩ መምህራኑ መሆኑን በተደጋጋሚ ይናገር ነበር፡፡ ትምህርቱን ካደላደለ በኋላም ምኞቱ በአንድ ሰፋ ባለ ገጠር ውስጥ ለተማሪ በሚመች አካባቢ በገዳም ወይም በደብር ተቀምጦ ቅኔ ለማስተማርና በዚያ ዕድሜው ለመግፋት ነበረ፡፡ ከቅኔ መምህርነቱ ባሻገር በምናኔና በድንግልና የመኖር ሐሳብ ነበረው፡፡

ለዚህ ምኞቱ ምሳሌ አድርጎ የወሰዳቸው ቅኔ ያስተማሩትን መምህራኑን የንታ አለቃ ማርቆስ ብርሃኑንና የንታ መምህር ያሬድ ዘመንግሥቱን ነበር፡፡ የነዚህን ከቡራንና ቅዱሳን አበው ፈለግ ስመከተል ከመመኘቱ ባሻገር በልጅነቱ ገድለ ቅዱሳንን በሚያስነብብበት ጊዜ የደናግሉና የመነኮሳቱ ታሪክ እጅግ አድርጎ ይመስጠው ስለ ነበረ ምኞቱ ሁሉ

የእነርሱን ፈለግ ለመከተል ነበር፡፡ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ከላይ በተጠቀሰው ቃለ ምልልስ ላይ እንዲህ ብሎ ነበር፡፡

"... በአንድ ገዳም ወይም በአንድ ደብር ተቀምጬ ብዙ ተማሪዎችን ማስተማር ነበረ ምኞቴ፡፡ በተለይም ቅኔ ማስተማር ደስ ይለኝ ነበር፡፡ ቤት ሠርቶ ከቤተሰብ ጋር ወይም በአስተዳደር ውስጥ እኖራለሁ የሚል ሐሳብ አልነበረኝም፡፡ ሐሳቤ በምናኔ መልክ በድንግልና፥ በንጽሕና ተወስኜ ለማስተማር ነበር፡፡ ብዙ አባቶች ነበሩኝ፡፡ በተለይም እዚያው ዲማ የነበሩ አለቃ ማርቆስ ብርሃኑ የሚባሉ ዓይነ ሥውር የመጻሕፍት የቅኔና የዜማ መምህር ነበሩ፡፡ እኔንም ለመጀመሪያ ጊዜ በቅኔ ሙያ ያበለጠኑኝ እርሳቸው ነበሩ፡፡ ከዚያም የንታ ያሬድ የምላቸው መንግሥቱ የነበሩ ታላቅ የቅኔ መምህር ነበሩ፡፡ እሳቸውም ዓይነ ሥውር አይደሉም እንጂ በተባሕትዎ፣ በንጽሕና፣ በድንግልና የኖሩ ናቸው፡፡..."
በማለት የቀደመ ምኞቱንና ሃሳቡን ገልጿል፡፡



# የከኛ ጭቃ ሹምነት

አባቴ የቅኔ መምህርነትንና ምንኩስናን አጣምሮ ለመያዝ በመወሰኑ ወደ ደብረ ሊባኖስ ሄዶ ምንኩስናን ለመቀበል ቁርጥ ሀሳብ አደረገ፡፡ ወንበር ዘርግቶ ወደ አስተማሪነት ከመግባቱ በፊት ደግሞ ወደ ዋድላና ወደ ጎንደር ሄዶ በዚያ ከሚገኙ ሊቃውንት ዕውቀትን ለመቅሰም ዝግጅት ማድረግ ፈለገ፡፡ በዚሁ መሠረት በጥር ወር ፲፱፻፴፮ ዓ.ም. ከጐጃም ወደ ደብረ ሊባኖስ አመራ፡፡ በጉዞው የዲማ ተማሪ የነበሩ አባ ወልደ ጊዮርጊስ የተባሉ ሰው አብረውት ነበሩ፡፡ በጐንደርና በዋድላ ለማድረግ ላሰበው ቆይታ ቀለብና ልብስ ያስፈልገው ነበረ፡፡ ስለዚህ የሚሆነውን ገንዘብ ማግኘትም አሳሳቢ ጉዳይ ስለነበረ ተጨማሪ የጉዞ ዓላማ ወጥኖ አዲስ አበባን የጉዞው መዳረሻ አደረገ፡፡

ከጐጃም ወደ አዲስ አበባ ባደረገው ጉዞ ቅድሚያ የሰጠው ማዕረገ ምንኩስና የመቀበሉን ጉዳይ ስለ ነበረ ወደ ደብረ ሊባኖስ አቀና፡፡ በዚያም ለተመሳሳይ ዓላማ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር የመጡ ሌሎች ሰዎችን አገኘ፡፡ ሥርዓተ ምንኩስና ለመቀበል በተያዘላቸው መርሀ ግብር መሠረት በዋዜማው በአንድ አካባቢ አድረው ጠዋት ሥርዓቱ ወደሚፈጸምበት ቦታ ተጠራርተው ለመሄድ ተስማሙ፡፡ ጠዋት ላይ ግን አባቴ ከባድ ዕንቅልፍ ጥሎት ኖሮ በሰዓቱ ሳይነሳ ቀረ፡፡ ባደኞቹም ዘንግተውት ሳይቀሰቅሱት ሄዱ፡፡ ከዕንቅልፉ እንደ ነቃ ወደ ቤተ ክርስቲያን ቢሄድ ሥርዓቱ ተፈጽሞ ቅዳሴም አልቆ ደረሰ፡፡ በዚያ የሚገኙ አንጋፋ መንፈሳውያን አባቶችም "የእግዚአብሔር ፈቃድ ባይሆን ነውና ተጨማሪ ጊዜ ወስደህ ፈቃደ እግዚአብሔርን ጠይቅ" ስላሉት ይህንኑ ምክር ተቀብሎ ቀጣይ ጉዞውን ወደ አዲስ አበባ አደረገ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ከአንዱ ደብር ወደ አንዱ ደብር እየተዘዋወረ ከጥር እስከ ግንቦት ድረስ ለአምስት ወራት ቆየ፡፡ በዚህ ቆይታው በትንሣኤ ዋዜማ በልደታ ቤተ ክርስቲያን ተገኝቶ ባቀረበው ቅኔ ተመሰገነ፡፡ በቅኔ ችሎታው የተደሰቱት ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ (በኋላ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ) በዓሉን ምክንያት በማድረግ ለሊቃውንቱ ባዘጋጁት ግብር ላይ

እንዲገኝ ጋበዙት፡፡ በግብዣው ሥነ ሥርዓት ላይም በችሎታው መደሰታቸውን ገልጠውለት ሠላሳ ማሪያ ቴሬዛ ብር ሸለሙት፡፡ በዚያው በሚያዝያ ወር በተከበረው በቅዱስ ጊዮርጊስ ዓመታዊ ክብረ በዓል ላይ በአራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተገኝቶ ቅኔ አበረከተ፡፡ በዚህ ዕለትም የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ መልአክ ገነተ ሀብተ ወልድ ዐሥር ማሪያ ቴሬዛ ብር ሸልመውታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በቤተ ክርስቲያኑ ግብር ቤት በቋሚነት እየተገኘ የዕለት ራቱን እንዲመገብ ፈቅደውለት ነበር፡፡ ለከተማው ባይተዋር ከመሆኑ በተጨማሪ ዓይነ ሥውርነቱ ኑሮን አክብዶበት ነበርና የዕለት ራት ማግኘቱ ለእርሱ ከፍተኛ ድጋፍ ነበረ፡፡

ከዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ጋር በልደታ ቤተ ክርስቲያን በተገናኘበት ወቅት ሌላ ቀን እንዲያነጋግራቸው ቀጠሮ ሰጥተውት ነበሩ፡፡ በዚሁ መሠረት ከቢሮአቸው ቀርቦ ወደ ዋድላና ወደ ጐንደር ሄዶ ትምህርቱን ለማስፋት ያለውን አሳብ ገለጠላቸው፡፡ አስከትሎም ለቀለቡ የሚሆን ጸረኀት እንዲፈቅዱለት ጠየቀ፡፡ እርሳቸው ደግሞ በከተማው የቅኔ መምህራን እጥረት መኖሩን ገልጠው ቅኔ እያስተማረ የሚፈልገውን ትምህርት እዚሁ አዲስ አበባ እንዲማርና በየወሩ ሠላሳ ብር ደመወዝ እንዲቆረጥለት ፈቃዳቸው መሆኑን ነገሩት። ሆኖም ግን የከተማውን ኑሮ ስላልፈለገው ፈቃደኛ ሆኖ ጥያቄአቸውን ሊቀበላቸው አልቻለም፡፡ በዚህ ምክንያት ላቀረበው የጸረኀት ጥያቄ መልስ ሠላሳ ብር ከጐጃም አገረ ስብከት እንዲሰጠው አዘዙለት፡፡

አባቴ ሠላሳ ብር እንዲያገኝ የተሰጠውን ፈቃድ ይዞ ወደ ጐጃም ተመለሰ፡፡ ብሩን አትራፊ ሥራ ላይ ለማዋልና ቋሚ አስተማማኝ ገቢ የሚያገኝበትን መንገድ ለማመቻቸት ፍላጐት ለለነበረው በጐችና ፍየሎች ገዝቶ የቅርብ ዘመዶቹ ዘንድ ለማኖርና እየተዋለዱ ሲበዙ በሽያጭ በሚገኘው ገቢ እራሱን እየረዳ ትምህርቱን ለመቀጠል ወሰነ፡፡

ምንም እንኳ እሱ ይሄንን ቢያስብም የሀገረ ስብከቱ ጽሕፈት ቤት ገንዘቡን በአንድ ጊዜ ሊሰጠው ፈቃደኛ ሳይሆን በመቅረቱ የታዘዘለትን ገንዘብ ዳረጐት አጠቃሎ ለመውሰድ ብዙ ጊዜ ፈጀበት፡፡ ይህንን ገንዘብ ለማግኘት በተራዘመ ቀጠሮ እየተጉላላ በነበረበት ወቅት ከአባቱ ወገን



በወረደው ባለአባትነት የኩኛ ባለ ጉልቶች የሚሾሙትንና በትውልድ ተራ የሚደርሰውን የጭቃ ሹምነት መሾም የእሱ ተራ ሆነ፡፡ ባህልና ወግ በሚፈቅደው ሥነ ሥርዓት መሠረትም ማዕረጉንና ኃላፊነቱን እንዲረከብ ከተወላጆች ጥያቄ ቀረበለት፡፡[20]

የጐጃም አገረ ስብከት ደጅ ጥናት እንደሚያቆየው የተገነዘበው አባቴ እዚያ አካባቢ መቆየቱ የማይቀር መሆኑን ሲረዳ የአገሩ የትውልድ ሥርዓት ያቀረበለትን ኃላፊነት ተቀበለ፡፡ የጭቃ ሹምነት ተራው የእርሱ መሆኑ በተገለጠበት ጊዜ ከሌላ ወደረኛ ባለአባት ተወላጅ የሆኑ ሰው ተራው የእኔ ወገን ነው የሚል ጥያቄ አነሱ፡፡ በስዚህ ጉዳዩ የጐጃም ባለአባቶችን ትውልድና ማንኛውንም ከሹመትና ከተወላጆች መብትና ግዴታ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በሚያየው ምክር ቤት እንዲታይ ተደረገ፡፡ በምክር ቤቱ ወሳኔ መሠረትም በጊዜው ኅጃምን ያስተዳድሩ ከነበሩት ከራስ ኃይሉ በለው ችሎት ቀረበ፡፡ ይህ ጉዳይ ችሎት በቀረበበት ዕለት አንድ ዘመነኛ የመንግሥት ሹም ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የኩኛን የጭቃ ሹምነትና ማዕረግ እንደ ኋላቀር ባሕል በማየት እያንቋሸሹና እያጣጣሉ አስተያየት ሰጡ፡፡ የፍርድ ቤቱ ሹም የአገሩን ሥርዓት፣ ወግና ልማድ ሳያውቁና ሳይረዱ የሚሰጡት አስተያየት ትክክል አለመሆኑን በመግለጥ አባቴ፤

"የኔ አገር የኩኛ ጭቅነት እርሰዎ እንደሚሉት ቀላል ጉዳይ አይደለም፡፡ የኩኛ ጭቅነት ለእግር ሲጠየፉት ለራስ የሚተርፍ ነው፡፡" የሚል ቅኔ ሰበበ መልስ ሰጠ፡፡ ይህን መልስ የሰሙት ራስ ኃይሉ በለው ደግሞ አባቴ ከሰጠው መልስ በመነሣት፣"እውነቱን ነው የኩኛ ባለአባትነትና ሹመት ታላቅ ነው፡፡ ብዙዎች ነገሥታት፣ እቴጌዎች፣ መኳንንትና

---

20 በጐጃም ለዘመናት ለዓዛ የኖረው የርስተ ጉልት ሥርዓት ህዝቡ በየአካባቢው ዳኞች የሚዳኝበትና ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትና ህዝብ የፈለገውን የሚሾምበት [illegible]

ወይዛዝርት የተገኙበት፥ እኛም የምንወለድበት ነው፡፡ ባለመለከረው የትውልድ ቅድሚያ መሠረት ተራው የእሱ በመሆኑ አጽንተንለታል" የሚል ፍርድ በመስጠታቸው ሹመቱ ጸደቀለት፡፡

የጭቃ ሹምነት ማዕረግ በተቀበለበት ቀን የማዕረግ ልብስ ለብሶ በታላቅ ሥነ ሥርዓትና የሀዝብ አጀብ ክብር የተደረገለት ሲሆን እሱም ባህሉ የሚፈቅደውን ከፍተኛ ግብዣ በማዘጋጀት ህዝቡን አስተናገዱል፡፡ አባቴ በጭቃ ሹምነቱ ኃላፊነት ላይ ብዙም ሳይቆይ በ ፲፱፻፴፰ ዓ.ም. የካቲት ወር ላይ ዘውዱ ብርሃኑ የተባሉ የቅርብ ዘመዱን ምስለኔ አድርጐ በመሾም ወደ አዲስ አበባ መጣ፡፡

# ምዕራፍ ፫

# የሐዋርያዊ ተልዕኮ ጅማሬ
# ፲፱፻፴፱ - ፲፱፻፵፱